# ምዕራፍ አሥራ ሁለት

# ፉክክርና ተቃውሞ

## የሃይማኖት ፉክክር

በ1943 ዓ.ም ወደ ሰሜናዊ ሲዳማ በደረስኩ ጊዜ አካባቢው በሃይማኖት በኩል የተራቆተ ሃይማኖት ያልገባበት ጊዜ ነበር:: እንዲያውም ሃይማኖታዊ ሰዎች የሉም ማለት ይቻላል:: ጥቂት የሃይማኖት አማራጮች የነበሩ ሲሆን፣ እኔ ከምሰብከው ያነሰና የተለየ ይመስል ነበር:: ሃይማኖተኞች ሁሉ ያልተሟላ ፍሊጋ ነበረባቸው:: እኔ ወደ እነርሱ በፉክክር መልክ አልተመለከትኩም::

ሰዎች ባህላዊ ሃይማኖታቸውን ከፈጣሪ ጋር ለማያያዝ ይሻሉ፣ ግን ምን እንደሆነ አያውቁም:: በምን ዓይነት አካባቢ እሰብክ እንደነበር ግንዛቤ እንድታገኙ ከነበሩት የሃይማኖት አማራጮች ጥቂቶቹን ልነግራችሁ እፈልጋለሁ::

ሁልጊዜ የኢየሱስ ቃል ይታወሰኛል:: በዮሐ. 15÷20 ላይ «ባርያ ከጌታው አይበልጥም ብዬ የነገርኋችሁን ቃል አስቡ:: እኔን አሳድደውኝ እንደሆኑ እናንተን ደግሞ ያሳድዱአችኋል፤ ቃሌን ጠብቀው እንደሆኑ ቃላችሁን ደግሞ ይጠብቃሉ» ይላል::

ይህንን ጥቅስ እስከ መጨረሻው አስታውሰዋለሁ:: ምክንያቱም ፉክክሩንና ተቃውሞውን ስትመለከቱ ታመሰግናላችሁ::

## የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን

በ1940ዎቹ ዓ.ም አካባቢ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ከነበረው መንግሥት የገንዘብና የአስተዳደር ድርሻ ነበራት:: በጊዜው የነበረው መንግሥት የአማራው የገገር መደብ ይባላል:: በዚያን ዘመን የአማራ ብሔር ያልሆነ ነገር ግን የኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን እምነት ተከታይ የሆነ ሁሉ ማህበራዊ እንቅስቃሴ ተቀባይነት ነበረው:: የኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን እምነት ተከታይ የነበረ ሰው ደህና ሥራ ለማግኘትና በህብረተሰቡ መካከል ብዙ ጥቅሞችን ለማግኘት ይችል ነበር:: በእያንዳንዱ የኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ማምለኪያ ቦታቸው የተሾሙ ካህናት ማለትም ቄሶችና ዲያቆናት ነበሯቸው:: ብዙውን ጊዜ እነዚያ ካህናት ከሲዳማ አካባቢ ውጪ የመጡ ነበሩ:: ራሳቸውንም ለክርስትና እምነት የአደራ አባቶች አድርገው ስለሚያዩ ሌሎች ቡድኖች ለምን ወደ እነርሱ እንደሚሄዱና በግልጽ እንደሚፎካከሩ አይረዱም:: በጅምራችን ላይ ካህናትና ዲያቆናት ብዙም አያስቸግሩንም ነበር:: ከወደኋላ በዚሁ ምዕራፍ ውስጥ በ1944 ዓ.ም ምን



እንደተከሰተ እነግራችኋለሁ:: የኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን መሪዎች ምን እንሠራ እንደነበር ስላልተረዱ የእኛን መገኘት ከፖለቲካ ጋር ያያይዙ ነበር::

ብዙውን ጊዜ የፖለቲካ ተቃዋሚዎችና አድመኞች አድርገው ስለሚገምቱ «የሚስዮን መንግሥት» ለመመሥረት እንደፈለግን አድርገው ያስወሩብን ነበር:: የካቶሊክ ሚስዮናውያን ከ1928 ዓ.ም ከጣሊያን ወረራ በፊት እንዳደረሱት ዓይነት ሁኔታ እንዳይፈጠር መፍራት ነበረባቸው ፤ (ያን ጊዜ ምን ተፈጥሮ እንደነበር ባስታሪኩ አላብራሩም):: እኛ ስለ ዘላለማዊ ፍርድ የምናስተላልፈውን ስብከት መንግሥት እንዳይረጋጋ ለማድረግ የምንጋብዝ አድርገው ይተረጉሙ ነበር:: በእርግጥ ስለ ፍርድ መጽሐፍ ቅዱስ ምን እንደሚል ጠንቅቀው ያውቃሉ:: ወደ ፖለቲካ ፈጥነው መተርጎማቸው እኛን ለማጥቃት ፈልገው ስለነበር ብቻ ነው:: በዚያን ጊዜ ቄሶችና ዲያቆናት ከመንግሥት ባለሥልጣኖች ጋር በጥብቅ እየተገናኙ ይሠሩ ነበር:: ያ ለእነርሱ ከባድ አልነበረም፣ ምክንያቱም የመንግሥት ባለሥልጣኖች ሁሉም የኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን አባሎች ስለነበሩ ነው:: የመንግሥት ባለሥልጣኖች ለቄሶችና ለዲያቆናት የእኛን ሥራ በመቃወም ቢደግፏቸውም በሁሉም ላይ ምንም ዓይነት ችግር አልፈጠርንባቸውም::

በኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያንና በእኛ ምዕመናን መካከል የነበረው ፉክክርና ጭቅጭቅ የእኛዎቹ ምዕመናን ታቦትን ተከትለው ስለማይወጡ ነው:: ታቦቱ የሚቀመጠው በቤተክርስቲያኑ ሕንፃ በመካከለኛው ክፍል ውስጥ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን የበላይ ተመልካችነት ነው::

በዚያን ጊዜ ማለትም በ1940ዎቹ ላይ የኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ተከታዮች በእኛ ላይ ለበብ ሲፈልጉ የሚጠይቁን ጥያቄ ስለ ታቦት ምን ታስተምራላችሁ? የሚል ነበር:: ብዙ አማኞች ተቃራኒ መልስ እየሰጡ አላስፈላጊ ችግር ለራሳቸው ይጋብዙም ነበር::

በ1955 ዓ.ም በእኛና በኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን መካከል ጠንካራ ግጭት ተነስቶ ነበር:: ለምን እንደሆነ ከወደኋላ እነግራችኋለሁ:: እኔ ሰባት ወር ከዘጠኝ ቀን የታሰርኩበትም ያን ጊዜ ነበር:: በእሥር ቤት በነበርን ጊዜ ለብቻችን የምንገለገልበትን ክፍል ስለሰጡን የእሥር ቤት ቤተክርስቲያን ለመመሥረት ችለናል:: የክፍለ ሃገሩ ማዕከላዊ እሥር ቤት ወደሆነው ወደ አዋሣ ባዛወሩን ጊዜም እዚያው ውስጥ ተመሳሳይ አገልግሎት እናከናውን ነበር::

ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ሰሜናዊ ሲዳማ በደረስኩ ጊዜ በዳምባራ ኬላ አንድ የኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ነበር:: የቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን ነው መሰለኝ በዚያ ቦታ ዛሬ ብዙ ሰዎች በኢየሱስ ክርስቶስ አምነዋል:: የቀድሞ የኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን በዚያ ቦታ ዛሬ ያለ አይመስለኝም:: ሌላው

የኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን በሲዳማና በጉጂ ድንበር ሼሎ በሚባል ቆላማ አካባቢ የነበረ ነው። ስሙን አላስታውስም። ትልቁ የኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን በአጠገባችን በለኩ ከተማ የሚገኘው የቅዱስ ጊዮርጊስና የሚካኤል አብያተ ክርስቲያን ናቸው።

በመንፈሳዊ ረገድ በእኛ ምዕመናንና በኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች መካከል ሁልጊዜ አለመግባባት ነበር። ለእነርሱና ለእኛ የግጭታችን መነሻ የቤተክርስቲያን ትምህርት አልነበረም። ትልቁ ነጥብ ተራው ሕዝብ የሚያምነው ነገር ነው። ብዙዎቹ የሚያምኑት ሰው ወደ እግዚአብሔር የሚቀርበው በድንግል ማርያምና በመላዕክት አማላጅነት ነው በማለት ነው። እኔም ከመጽሐፍ ቅዱስ እየጠቀስኩ ሰዎች ወደ እግዚአብሔር ሊቀርቡ የሚችሉት በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ብቻ እንደሆነ አስተምሬአለሁ። ዮሐ. 10÷9 ሰዎች ደህንነትን የሚያገኙት በክርስቶስ በኩል ብቻ ነው።

እንደሚታወቀው የኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን እምነት ተከታዮች በየሳምንቱ ረቡዕና ዓርብ ሥጋ፣ ቅቤና ዕንቁላል አይመገቡም። በሌሎችም ኢጋጣሚዎች በዓመት ውስጥ የሚጾሙባቸው ቀናቶች አሉ። ስለ ጾምና ስለ መጾም በእኛና በእነርሱ መካከል በሃሳብ አለመግባባት አለ። ነገር ግን መጾማቸው ከባህል ጋር የተያያዘ ነው እንጂ በመጽሐፍ ቅዱስ የተደገፈ አይደለም። ስለዚህ በሃሳብ ሳንግባባ ስለምንቀር ያ አለመግባባት ከብርሃን ይልቅ ትኩሳትን ያባብስ ነበር። ደግሞ በብሉይ ኪዳን የተጻፈው ሁሉ ለአንድ ብሔር /ለእሥራኤላውያን/ ለተወሰነ ጊዜ የተሰጣቸው መሆኑን ልናሳያቸው እንሞክር ነበር። የተለያየ ሃሳብ ሰላለን ስለ መጽሐፍ ቅዱስና ትርጓሜው ስንነጋገር ወደ መልካም መግባባት ልንደርስ አልቻልንም።

## እሥልምና

በ1943 ዓ.ም ወደ ሰሜናዊ ሲዳማ በደረስኩ ጊዜ ብዙ የሲዳማ ሰዎች ሙስሊሞች ነን ይሉ ነበር። የአረቢኛ ቋንቋ አይናገሩም። በቀን አምስት ጊዜ አይሰግዱም፣ ነገር ግን ከሰይጣን እሥራት የተፈቱ እየመሰላቸውና የእስልምና መሪዎች ከሰይጣን ባርነት ለማውጣት ቃል ስለሚገቡላቸው ነው። ለሲዳማ ሕዝብ ያን ጊዜ የእስልምና እምነት አማራጫቸው ነበር። ከሙስሊሞች ጋር በንግድና በጋብቻ ብዙ ሲዳማዎች አልተቆላለፉም። በደጋማው አካባቢ የተወሰኑ መስጊዶች ተሠርተው ነበርና ሁሉም የተለዩ ቀናት ነበሯቸው። ያን ጊዜ ሙስሊሞች ወደተሰበሰቡበት እየሄድን ወንጌልን እንድንሰብክላቸው ይፈቅዱ ነበር።

ሰዎች ስለምናስተምረው ትምህርት ትኩረት ይሰጡ ስለነበር፣ ብዙ ሕዝብ ወንጌልን ለመስማት ችሏል። ሙስሊሞች ስለምንሰብከው ወንጌል የተለያዩ



ጥያቄዎችን ያቀርቡልን ነበር። በመጨረሻ ግን በየስብሰባዎቻቸው ልንሰብክ ስንፈልግ ዝም ሊሉን አልቻሉም።

በአካባቢው ጥቂት ሼኪዎች ነበሩ። ብዙዎቹ ከአላባ አካባቢ የመጡ ነበሩ። በጠቅላላው በሲዳማ የእስልምና ሃይማኖትን የሚከተሉት በማስመሰል ራሳቸውን ሲያታልሉ ይስተዋሉ ነበር።

በ1940ዎቹ አጋማሽ ላይ መንፈሳዊ ተጓዦች ነበሩ። ግን እንደ ዛሬው ብዙ አልነበሩም። እነዚያ ተጓገሮች መንፈሳዊ በዓላቸውን ለማክበር በባሌ ክፍለ ሃገር ይገኙ ነበር። በሲዳማ ወንጌል እንደተሰራጨ ብዙ ሰዎች በኢየሱስ ክርስቶስ አምነዋል። አብዛኛዎቹ ሙስሊሞች በከተማዎች ነበሩ። አብዛኛ ዎቻቸውም ለቡና ንግድ የመጡ የጉራጌ ጐሳዎች ነበሩ። በሲዳማ ሙስሊሞች የፖለቲካ ሥልጣን አልነበራቸውም። የመንግሥት ባለሥልጣኖችም አልነበሩም። ከቄሶችና ከዲያቆናትም ያነሰ ክብር ነበራቸው። ሙስሊሞች እኛን ለመቃወም በሚፈልጉበት ጊዜ የመንግሥት ባለሥልጣኖች ከጐናቸው ስለማይቆሙ ገፍተው አይቃገሉንም ነበር።

ከሙስሊሞች ጋር በምንነጋገርበት ጊዜ የምንጠቀመው ዘዴ እስቲ ስለ ኃጢአትና ስለ ደኅንነት ቁርአን ምን ይላል? ብለን መጠየቅ ነው። የእነርሱን ሃሳብ ከሰማን በኋላ መጽሐፍ ቅዱስ ምን እንደሚል እንነግራቸው ነበር። ክርስቲያኖች በዚህ ዘዴ ከሙስሊሞች ጋር በመነጋገር መልካም ውጤት ያለውን ውይይት ያካሂዳሉ እንጂ ባለመግባባት አይቋጩም ነበር።

## የተዋረድ ሃይማኖተኞች

እንደዚህ ዓይነት ሰዎች በሲዳማና በሌሎችም ቦታዎች የሚገኙ ሲሆን፣ እነርሱም ከቤተሰቦቻቸው ሲወርድ ሲዋረድ የመጣውን ሃይማኖት የሚከተሉ ናቸው።

በብዙ ምክንያቶች እነዚህ ሰዎች ከእግዚአብሔር ጋር ግንኙነትን ቢፈልጉም እንኳን እኛ እንረዳችኋለን በሚሉ ሰዎች እየታገዱ እውነተኛውን አምላክ ለማግኘት ተስኗቸዋል። ያ ሃይማኖት ክፉ ነገርንና መከራን እናሳልፍልሃለን እያሉ የሚጋብዙበት ነው።

እነዚያ ሰዎች የቃልቻዎችን ወይም የሰይጣን ሠራተኞችንና የካህናትን ትዕዛዝ የማይፈጽም በሽታና ሞት እንደሚመጣበት በመዛት ይነግሩታል። ያንን የባሕል ተጽዕኖ ለመጋፈጥና ድል ለማድረግ ጠንካራ የእምነት ሰው መሆን ያስፈልጋል።

ሰዎች ትዕዛዛቸውን ባለመፈፀም በኢየሱስ ክርስቶስ አምነው ሲለወጡ በራሳቸው፣ በንብረታቸውና በከብቶቻቸው ላይ የሚደርስባቸው ክፉ ነገር

አልነበረም:: በተጨማሪም ያመኑትን ሰዎች የተለወጠ ሕይወት በመመልከት ሰይጣንና አገልጋዮቹ አንዳች ጥፋት ለማድረስ ኃይል የሌላቸው መሆኑን እየተመለከቱ ሌሎች በርካታ ሰዎች በክርስቶስ ለማመን ችለዋል:: ከረዥም ጊዜ ቆይታ በኋላ ሰይጣንን ያገለግሉ የነበሩ ቃልቻዎችም በኢየሱስ ክርስቶስ አመኑ:: በ1940ዎቹ አካባቢ ሺፎ የሚባል ኃይለኛ ሰው ነበር:: ሌሎች እንደ እግዚአብሔር ይቆጥሩትም ነበር:: እርሱ የሚያዛቸውን ትዕዛዝ ካልፈጸሙ እንደሚሞቱ በመግለጽ ሰዎችን እያስፈራራ ያጠቃቸው ነበር::

ብዙ ሰዎች ለክብሩ ይዘፍኑለታል:: ሳያቋርጡም ገንዘብ እንደ ቀረጥ ይከፍሉት ነበር:: ለእርሱ በድፍረት ሄደን ወንጌልን በሰበክንለት ጊዜ አሳስሮን ጥቂት ቀናት አቆየን፤ ብዙም ሳይቆይ በድንገት ታሞ ሞተ:: ከቤተሰቦቹ ብዙዎቹ ዛሬ በኢየሱስ ክርስቶስ የሚያምኑ ሆነዋል::

ሌላው ኃይለኛ የነበረ ሰው ብራዶ ይባላል:: እርሱም በጊዜው የብዙ አካባቢዎችን ሕዝብ ተቆጣጥሯል:: ብዙውን ጊዜ የተለያዩ ምክንያቶችን እየሰጠ ሰዎች ከብቶቻቸውን እንዲያርዱለት ይጠይቅ ነበር:: እርሱም ሰይጣንን ተግቶ ሲያገለግል በድንገት ታሞ ሞተ:: እነዚያን ሰዎች ኃይለኛ ያደረጋቸው ዋናው ምክንያት የሲዳማ ሕዝብ ለሙታን አባቶች መንፈስ የሚያሳየው ፍርሃትና አምልኮ ነው:: ሲዳማዎች የሙታን መንፈስ ኃይለኛና አደገኛ ስለሆነ በእኛ ላይ ክፉ ነገር እንዳያደርስብን በሚቻለን ሁሉ ልናስደስተው መቆም አለብን የሚል እምነት ነበራቸው:: የሰይጣን አገልጋዮች /ቃልቻዎችም/ በሰዎች ላይ ያላቸውን ኃይል በይበልጥ ለማሳወቅ ለሙታን መንፈስ ከብቶቻቸውን እያረዱ እንዲሰጡ ሳያቋርጡ ያሳስቡ ነበር:: ብዙ የሲዳማ ሕዝብ ከዚህ ፍርሃት ለመላቀቅ ይፈልጋል:: እንደዚህ ዓይነት ባህል ቀድሞ የነበረ ሲሆን፣ ዛሬ በመላው ሲዳማ ከስሟል ለማለት ይቻላል::

ከዚያም ከሰይጣን እሥራትና ባርነት ያላቀቃቸው የወንጌል መስበክና የሕዝቡም ለቃሉ መታዘዝ ነው::

ሁሉም እንደሚገምተው የእንደዚያ ዓይነት የባህል እምነት የሲዳማን ሕዝብ ምጣኔ ሀብት እጅጉን ጐድቶቷል:: ምክንያቱም የወተት እንስሳትና የእርሻ በሬዎች ሁሉ ለመስዋዕትነት በየጊዜው ስለሚታረዱ፣ ሕዝቡ ለድህነት ተዳርጐ ኖሯል:: ቃልቻዎች በእኛ ላይ ሰበብ በሚፈልጉበት ጊዜ ወይም ተቃውሞ ሊያስነሱብን ሲፈልጉ የመንግሥት ባለሥልጣኖችን ያስነሱብን ነበር:: እነዚያ ሰዎች በተለይም በጣም ኃይለኞች የነበሩት ሴቶች ሲሆኑ፣ የፖለቲካ ጥገኛ ያልሆኑና በራሳቸው ሃሳብ የሚመሩ ናቸው:: የእነርሱ ሁከት መፍጠር እኔን አያስፈራኝም ነበር:: ከእነርሱ ምንም ማስጠንቀቂያ አይደርሰኝም፣ በፍፁም ጐድተውኝም አያውቁም:: ይህም የሚያረጋግጠው



ቃልቻዎችና መሰሎቻቸው በክርስቲያኖች ላይ ኃይል የሌላቸው መሆኑን ነው:: ሌሎቹ ወንጌል እንዳይሰበክ ለማገድ የሚሞክሩት የመሬት ባላባቶች ነበሩ::

## የመሬት ባላባቶች

የመሬት ባለቤትነትን የበላይ ሆነው የተቆጣጠሩት «የመሬቾ» የተባሉ የሲዳማ ጐሳዎች ናቸው:: እነርሱም የመሬት ከበርቴ ተወካዮች ናቸው:: ይህም በገጠሩ አካባቢ ሕጋዊ ያልሆነ መሪነትን እንዲይዙ አድርጓቸዋል:: በተጨማሪም ከመንግሥት አስተዳደር ባለሥልጣኖች ጋር ቅርበት የነበራቸው ናቸው::

የመሬቾ የተባሉ የሲዳማ ጐሳዎች የገጠሩን ሕዝብ ከሚያስተዳድሩ የመንግሥት ባለሥልጣኖች ጋር አለመግባባት እንዲፈጠር አይሹም:: የመሬቾዎች ለማንም ተጠያቂና ሃላፊ አይሆኑም:: ነገር ግን ለራሳቸው ደስ የሚላቸውን ያደርጋሉ::

በ1940ዎቹ በሲዳማ ባርነትን የማሳየት አዝማሚያ በፍፁም አልነበረም:: እንደ እውነቱ ከሆነ ግን ብዙ ሰዎች የመሬቾ ለሆኑት እንደ ባርያ ያገለግሉ ነበር:: የራሳቸው ሕይወት አልነበራቸውም:: የመሬቾ የሆኑ ሰዎች ካዘዙአቸው ከብቶቻቸውንና እህላቸውን ሳይቀር ማስረከብ ነበረባቸው:: ለሥራ ተፈልገው ሲጠሩ ሄደው የመሥራት ግዴታ ነበረባቸው:: ሰዎቹ ባሪያዎች አይባሉም፣ ነገር ግን እንደ ባሪያ ስለሚያሰሯቸው ብዙዎቹ ራሳቸውን እንደ ባሪያ እንዲቆጥሩ አድርጓቸዋል::

የመሬቾዎች ቆሮ የሚባል ተወካይ ነበራቸው:: እነዚያም ቆሮዎች የየመሬቾዎችን የበላይነት ላልተወሰነ ጊዜ የሚቀጥል አድርገው ስለሚያምኑ የተወከሉ ናቸው:: ቆሮዎቹ ከበላዮቻቸው ምንም ገንዘብ አይቀበሉም ነበር::

ስለዚህ ጥሩ አምራች ገበሬ ለመሆን እጅግ የሚከብድ ነበር:: እኔንና ሌሎቹን ወንጌላውያን ለምን ይቃወሙናል? የእነዚያን ባለሥልጣኖች ኪስ ለመሙላት ምን ማለትና ምን ማድረግ ነበረብን? እንደ ደንቡ ከሆነ የመሬቾዎችና ቆሮዎች በጣም ብዙ እህልና ከብቶች እንዲሁም ገንዘብ ከተራ ገበሬዎች አይቀበሉም:: ገበሬዎች በበኩላቸው የኢትዮጵያን ሕግ የሚረዱ ቢሆንም፣ ስለ እነዚያ የመሬቾዎች ግን በግል የወጣ ሕግ ባለመኖሩ የሚያውቁት ነገር አልነበረም::

ሰዎች በመጀመሪያ መንፈሳዊ ነፃነትን አትርፈዋል:: ቀጥለውም መጻፍና ማንበብ ችለው መብታቸውን አውቀዋል:: ከዚያም የአካባቢው ባለሥልጣኖች ስለሚያሳድሩባቸው ተጽዕኖ ማጉረምረም ጀምረዋል:: ያንን አዝማሚያ ባለሥልጣኖቹ አልወደዱላቸውም:: ክርስቲያኖች ቅሬታቸውን በህጋዊ መንገድ ለመንግሥት አስተዳደር ማቅረብ ሲጀምሩ፣ በሕጉ መሠረት የመንግሥት

አስተዳደር ከክርስቲያኖቹ ጐን ይሆናል። ይህንን የአካባቢው ባለሥልጣኖች አይወዱም። ከዚህም የተነሳ በክርስቲያኖችና በአካባቢው ባለሥልጣኖች መካከል ግጭት ሲፈጥር ኖሯል።

ከብዙ ዓመታት በኋላ ህዝቡ ከምጣኔ ሀብት ባርነት ነፃ ወጥቶአል። የመሬቹና ቆሮ የሆነ ሰው ወደ ፍርድ ቤት ይወሰዳል ማለት ዘበት ነው። ይህ በሲዳማ ታሪክ በፍጹም ያልሆነ ነበር። እነዚያ ባለሥልጣኖች ስህተታቸውን ስለሚያውቁ ስለ መብታቸው እንኳን አይሟገቱም።

ክርስቲያኖች ግን ሕግ ከጐናቸው መሆኑን ስለሚያውቁ፣ የአካባቢ ባለሥልጣናትን ወደ ፍርድ ቤት ያስወስዷቸዋል። በአብዮታዊ ለውጥ ወቅት ከ1966-1983 ዓ.ም የመሬቾዎች ከነበራቸው የበላይነት ብዙም አልተለወጡም።ነገር ግን በአፄ ኃይለሥላሴ ዘመን ያላቸውን ያህል በሕዝቡ ላይ በግልጽ ተፅዕኖ ማድረግ ዛሬ አልቻሉም።

መንግሥት መሬት ለማከፋፈል ሞክሮ የነበረ ቢሆንም፣ እነዚያ ሰፊ መሬት የነበራቸው የመሬቾዎች አሁንም መጻፍና ማንበበ በማይችል የገጠሩ ሕዝብ አካባቢውን እንደተቆጣጠሩት ነው። በገጠር ሌሎች ሁለት ቡድኖች ነበሩ። እነርሱም ከተወዳዳሪዎች ጐራ ያልሆኑና የሲዳማ ሰዎችም ያልነበሩ ናቸው።

## አማሮች

አብዛኛዎቹ እንደ ዳምባራ ኬላ ባሉት ከተሞች የነበሩ በጊዜው ታዋቂ የመንግሥት ባለሥልጣኖች የነበሩት አማሮች ነበሩ። ሁሉም ማለት ይቻላል፣ ወታደሮች የነበሩና ጡረተኞች ሲሆኑ፣ በሰሜናዊ ሲዳማ አነስተኛ ከተማ ውስጥ ሰፍረው የሚኖሩ ናቸው። በጣም ጥቂቶች ብቻ በገጠሩ አካባቢ ይኖራሉ። በእርሻ ለመተዳደር ፍላጐት አልነበራቸውም። ሁሉም የኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን እምነት ተከታዮች ሲሆኑ፣ ሌሎች ሰዎች ካልገፋፉአቸው በስተቀር በወንጌል ስብከታችን ተቃውሞ አያሰሙም።

ብዙ ዓመታትን አብረን ካሳለፍን በኋላ ብዙዎቻቸው የእውነትን ወንጌል ሰምተው ጌታ ኢየሱስን እንደ ግል አዳኛቸው አድርገው ተቀብለውታል።

## ጉጂዎች

የጉጂ ጐሳዎች በቆላማው ምድር ከብላቴ ወንዝ አጠገብ የሚኖሩ ናቸው። ጉጂዎች ከሲዳማዎች ጋር በነፃነት ተቀላቅለው ሲኖሩ፣ ብዙውን ጊዜ በጋብቻ አይተሳሰሩም።



ብዙ የጉጂ ጐሳዎች ወንጌልን ሰምተው በኢየሱስ ክርስቶስ ያመኑ ቢሆንም፣ ከሲዳማዎች ጋር በነፃነት ስለሚኖሩ በሰሜናዊ ሲዳማ አብረው ከማምለክ ውጪ የጉጂዎች ቤተክርስቲያን ተለይቶ አልተመሠረተም።

ብዙ ጉጂዎች ለቤተክርስቲያን ዕድገት ጥሩ ሚና ተጫውተዋል። በሰሜናዊ ሲዳማ ወደ ደቡባዊ ጠረፍ ርቀው የሚኖሩ ጉጂዎች ከሲዳማዎችና ከወላይታዎች ጋር አይገዳደሉም፣ ከሁለቱም ወገን ጋር በሰላምና በነፃነት ይኖራሉ።

ብዙዎቹ የወላይታ ወንጌላውያን በጉጂ ሕዝብ መካከል ወንጌልን አሰራጭተዋል። አላር የሚባለው ወንጌላዊ ሰረኘርም ዓመት በመካከላቸው ኖሮ ሰብኳል። አየለም ሌላው በመካከላቸው ለብዙ ጊዜ ያገለገለ ወንጌላዊ ነው።

ጉጂዎች የራሳቸውን ቋንቋ ይጠቀማሉ። የሲዳሚኛ ቋንቋንም በደንብ ይናገራሉ። ብዙዎቹ ነጋዴዎች ስለነበሩ በአማርኛም መነጋገር ይችላሉ።

አብዛኛዎቹ አራቱንም ቋንቋዎች በደንብ አቀላጥፈው መናገር ይችላሉ። የጉጂዎችን ሃይማኖት በቅርብ ሆኜ ባላጠናም ከሲዳማዎች የተለየ አይመስለኝም። ጥቂቶቹ ሙስሊሞች ሲሆኑ፣ በሲዳማ አካባቢ ወዳሉ መስጊዶች ይሄዳሉ።

## የመጀመሪያው ሕጋዊ ተቃውሞ

በ1943 ዓ.ም አንድ እሁድ ጧት ከዳምባራ ኬላ ከተማ የመጡ የመንግሥት ባለሥልጣኖች ወደምናመልክበት ቤተክርስቲያን መጥተው ወሰዱንና አሰሩን። «ወደ ፖሊስ ጣቢያ ሄደህ ለምንጠይቅህ ጥያቄዎች መልስ ትሰጠናለህ» አሉኝ። ያኔ እንደዚያ ብለው በመውሰድ ያስሩ ነበር።

ከዚያም ከአካባቢው ሊያስወጡን እንደሚፈልጉ ነገሩን ፤በዚያ እሁድ ጧት ሌሎች አምስት ሰዎች በአገልግሎት ላይ ነበሩ። እነርሱም ቃሬሶ፣ ባጥሶ፣ አታሮ፣ ቦኩ፣ እና ወዬሳ ሲሆኑ፣ ስድስታችንንም ለጥያቄ ብለው ወሰዱን።

በአንድ የመስቀልኛ መንገድ ላይ እንደደረስን ወደ ቤተክርስቲያን መሄድ ካቆምን እንደሚለቁን ነገሩን።

## ክሶች

ሊያስሩን የሚችሉት የክስ ምክንያት ሲኖራቸው ብቻ ነው። የክስ ምክንያታቸው ሕዝቡን ሰብስበው እርሻችሁን አትረሱ ፣ ወደ ገበያ መሄድ አያስፈልጋችሁም ይላሉ፣ ሃይማኖትን ያጠፋሉ፣ ሰዎች ከብቶቻቸውን

እንዳይንከባከቡ በጠቅላላው ገጠር አካባቢ ብጥብጥና ዐመፅ ይናኛሉ የሚል ነበር።

ባለሥልጣኖች ሁሉም የወንጌል ስብከታችንን ለብዙ ጊዜ ሰምተዋል። የእኛ ንም ማንነት በደንብ ስለሚያውቁ የቀረበብን ክስ እውነት አለመሆኑን በሚገባ ተረድተዋል። ቢሆንም ስለ እኛ ማንነት ማወቃቸው ለእኛ ምንም አልጠቀመንም።

በገጠር ቆሮ ተብለው የተሾሙት ሁሉ ከአንደበታችን ወንጌልን ለብዙ ጊዜያት ሰምተዋል። በመጨረሻ እንዲያውም የአንድ ቆሮ ልጅ በክርስቶስ አምኗል።ከመጀመሪያው ጀምረን በሳምንት ሁለት ቀን ተሰብስበን በቤተክርስቲያን ለአገልግሎት የመገናኘት ልምድ አካብተናል። በየሳምንቱ ሐሙስ ከጧቱ ሁለት ሰዓት እስከ አምስት ሰዓት፣ እንዲሁም በየሳምንቱ እሁድ ከሦስት ሰዓት እስከ ስድስት ሰዓት የአምልኮትና የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናቶች አሉን።

የአካባቢ ባለሥልጣኖች እሁድ እለት ከፈለጉን የት እንደምንገኝ ያውቃሉ። በጧት መጥተው ከቤተክርስቲያን የያዙንም ለዚሁ ነበር።

እኛ ማንነታችንን ለመደበቅ ያደረግነው ጥረት አልነበረም ። በየጊዜው ቃሉን እየሰበክን በሕዝቡ መካከል ስንዘዋወር እንታወቃለን። ከያዙን በኋላም በዳምባራ ኬላ ከተማ ውስጥ ወደሚገኘው ፖሊስ ጣቢያ አድርሰውን ለስድስት ቀን አሰሩን። ቀጥለውም ለኩ ወደሚገኘው ትልቁ ፖሊስ ጣቢያ ወሰዱን።

## ለእሥር ቤት መክፈል

በዚያን ዘመን አንድ እስረኛ ለመታሰር ሲገባ የመግቢያ ገንዘብ ይከፍል ነበር። ይህ የሚከፈለው የመግቢያ ገንዘብ በተዘዋዋሪ መንገድ ጉቦ መሆኑ ነው። የሚሰጥበትም ምክንያት ታሳሪው በጥበቃ ፖሊሶች ድብደባ እንዳይደርስበት የሚሰጥ የእጅ አዙር ጉርሻ ነው።

እኛ ምንም ገንዘብ እንደሌለንና አንዳች ልንከፍል እንደማንችል ለፖሊስ ጣቢያው አዛዥ አስቀድመን ብንነግርም አዛገዩ በጣም ተቆጡን። የአዛገዩ ቁጣ እኛን ለመቅጣት ምልክት መሆኑ ገብቶናል። ምክንያቱም የምንከፍላቸው የጉቦ ገንዘብ እንደሌለንና ምንም ለማድረግ እንደማንችል በመናገራችን ነው።

ዝም ብለን በመቆየት ምን ዓይነት ከባድ ቅጣት እንደሚያደርሱብንና እንዴት እንደሚያስተናግዱን መጠበቅ ጀመርን። ከቤተክርስቲያን መጥተው ሲወስዱን የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱሳችንን እንድንይዝ ፈቅደውልን ነበር። ስድስታችንም መጽሐፍ ቅዱሳችንን ይዘናል። መጽሐፍ ቅዱሳችን ቅዱስ



በመሆኑ ለማንቋሸሽ አይሞክሩም ነበር። መጽሐፍ ቅዱሳችንን እንድንይዝ የፈቀዱልን ወንጌልን ስንሰብክ ያገኙን መሆናቸውን ለማስረገጥ ነው።

ደግሞም ከአለታ ወንዶ ኤስ አይ ኤም ሚስዮን የተሰጠንን የድምፅ መቅረጫ ቴፕ እንድንይዝ ስለተነገረን ይዘን ነበር። በዚያ ቴፕ ውስጥ በአማርኛ ና በሲዳሚኛ ቋንቋ የተሳለፉ የወንጌል ስብከቶች ነበሩበት። ቢሆንም የመንግሥት ባለሥልጣኖች የኤስ አይ ኤም ሚስዮን ያንን ቴፕ እንዳያድልና ማንም እንዳይጠቀም ከልክለው ነበር።

## ሁካታ

ወደ ለኩ እሥር ቤት ሁኔታችን ልመልሳችሁ። በዚያን ምሽት በስድስት ሰዓት አካባቢ የጥበቃ ፖሊሶች አመፀኛ እጃቸውን ክፉኛ አሳረፉብን። ነፍሳችን ልትወጣ ጥቂት እስኪቀራት ድረስ ስድስታችንንም ደበደቡን።

እኛን ለመደብደብ በአቀዱ ጊዜ ያቀረቡት ምክንያት ከእሥር ቤት ሊያመልጡ ሲሞክሩ ደረስንባቸው የሚል ነበር። ሆን ብለው ግርግርና ትርምስ ሲፈጥሩ፣ አንዱ ፖሊስ በሳንጃ የወጋኝ ጠባሳ እስከ ዛሬ በግራ ክንዴ ይታያል።

በረብሻው በጣም የተጐዱት በከና አታሮ ነበሩ። እንዲያውም በአንድ ወቅት አታሮን ገድለውታል ብለን ነበር። በጨኸቱ መኻል ወዬሳ ከባድ የዱላ ምት ከደረሰበት በኋላ ሊያመልጥ ችሏል። አንድ እሥረኛ ማምለጡን የተገነዘቡት ፖሊሶች በቀረነው እሥረኞች ላይ የድብደባ ሥቃይ አበዙብን። ዘበኞቹም በኃይል ይጮሁብን ነበር።

አደገኛው እስረኛ አምልጧልና እርዱን እያሉ ከተማውን ለሦስት ሰዓት ያህል እየዞሩ ያስተጋቡ ነበር። በምሽት ጨለማን ተገን በማድረግ ወዬሳ ወደ አለታ ወንዶ ኤስ አይ ኤም ሚስዮን ግቢ በመድረስ የደረሰባቸውን ችግር ለሚስዮኑ ሃላፊ ዴልማር እስቲቨንስ ነገራቸው። ያንን ማድረጉ ከረዥም ጊዜ በኋላ እንድንፈታ ቢረዳንም በዚያ በአጭር ጊዜ ግን ተጨማሪ ሰንበር እስኪታይብን ድረስ ደብድበውናል።

የጐረበጠውንና ሰንበር ያወጣውን ሰውነታችንን ከሸፈኑን በኋላ በሰንሰለት አሰሩን። ሁሉቱ እግሮቹም በሰንሰለት ተጠፈሩ። አምስታችንንም በሁለትና በሦስት ከፋፍለው በእግር ብረት አሰሩን። እንደታሰርን በለኩ ስድስት ቀን አሳለፍን። እንደ እኛ ያሉትን ሰዎች በእግር ብረት ማሰር ከሕግ ውጪ ቢሆንም፣ በዚያን ዘመን በገጠሩ አካባቢ ሕገወጥ ድርጊት የመሆኑ ትርጉም የገባው አልነበረም።

ከመካከላችን ደግሞ አንዱ ያመልጥ ይሆናል፣ በሚል ጥርጣሬ ልብሶቻችንን ገፍፈው ወስደዋል። እኔ ስስ ሸሚዝ ብቻ በአንገቴ ዙሪያ ጠምጥሜ ነበር። በዚያን ጊዜ ጫማ ስለማናደርግ ሊቀሙን አልቻሉም። አንድ ቀን በምንፈታበት ጊዜ ልብሶቻችንን መመለስ ስለሚኖርባቸው ከገፈፉን በኋላ በጥንቃቄ አስቀምጠውታል።

የጳውሎስ እናትና የበኩ ሚስት በየቀኑ ምግብ ያመጡልን ነበር። በዚያን ጊዜ ከእሥር ቤት የሚሰጠን ምግብ አልነበረም።

## እንደገና ማዛወር

የአካባቢያችን ባለሥልጣኖች ምን እንደሚያደርጉን ግራ ስለገባቸው ሊፈቱንም ስላልፈለጉ የክፍለ ሀገሩ እሥር ቤት ወደሚገኝበት ወደ ይርጋለም ሊያዛውሩን ወሰኑ።

በለኩ እሥር ቤት በነበርን ጊዜ ግን ወንጌልን ለመስበክ በጣም አመቺ ጊዜ ነበረን። ስለ እኛ ማንነት የማያውቁ ብዙ ሰዎች እነዚያ አደገኛና ችግር ፈጣሪ የተባሉት ሰዎች እነማን እንደሆኑ እንያቸው ተባብለው ሊያዩን ይመጡ ነበር።

በፖሊስ ጣቢያ የነበሩ ሰዎች ወንጌልን እንዳንሰብክና ቴፖቻችንን እንዳናዳምጥ አልከለከሉንም። በየጊዜው የተለያዩ ሰዎች ይመጣሉ፣ እኛም ወንጌልን እንሰብካለን። በለኩ እሥር ቤት ለብዙዎቹ ወንጌልን ብናሰማም በወቅቱ ግን በክርስቶስ ያመነ አልነበረም።

ወደ ይርጋለም እሥር ቤት በደረስን ጊዜ የወህኒ ቤቱ ሃላፊ /ስሙ ፀሐይ ይባላል መሰለኝ/ ባየን ጊዜ በጣም ተረበሸ። ከለኩ ያመጣንን ፖሊስ ስለ እኛ እንዲገልጽለት በትዕዛዝ መልክ ጠየቀው። ፖሊሱም በገጠሩ አካባቢ ሁከት የሚፈጥሩና ሚሽን የሆኑ ናቸው ብሎ ገለፀ።

ፀሐይ ጥሩ ክፍል እንዲሰጡን ለጥበቃ ፖሊሶች ቢነግርም፣ ፖሊሶቹ ከጉናችን የቆሙና ያደሉልን እንዳያስመስልባቸው ስለፈሩ አዛዡ ራሱ የተሻለ አነስተኛ ክፍል በወህኒ ቤቱ ዳር አገኘልን። ክፍሉ ንፁህ አየር የሚገባበት ቢሆንም፣ ወለሉ ግን በጠጠር ድንጋይ ከመሞላቱ የተነሳ ክፍሉ በሙሉ ቁኒን የተራባበት ነበር።

ልክ እንደ ጉንዳን የበዛ ትኋን ክፍሉን ሞልቶታል። ዘበኞቹም የምናነጥፈውን ኬሻ አንሰጥም አሉን። ለእሥረኞች ቀላሉን ነገር ኬሻን መከልከል የበለጠ ሊያሰቃዩን እንደሆነ ይታወቃል።

ገንዘብ ከተከፈላቸው ግን የተሻለ ቦታ መስጠት ይችላሉ። ለጉቦ የምንሰጠው ገንዘብ አልነበረንምና መሰቃየታችን አልቀረም። በዚያን ጊዜ በሲዳሞ ክፍለ ሀገር ውስጥ ስድስት ወረዳዎች ነበሩ። እኛን የክፍለ ሀገሩ



እሥር ቤት ወደ ይርጋለም በወሰዱን ቀን የስድስቱም ወረዳ አስተዳዳሪዎች ለስብሰባ ተጠርተው ወደ ይርጋለም ገብተዋል።

የእሥር ቤቱ ሃላፊ ስለ እኛ መታሰር አንስቶ ነገራቸው። እነዚህ ወንጌላውያን ያደረሱት ችግር ምንድን ነው? ለማወቅ እፈልጋለሁ አላቸው። እነዚህ ሚሽኖች ከለኩ ተልከው ወደ እኔ ደርሰዋል አላቸው።

## በዳኛ ፊት

በሚቀጥለው ቀን የክፍለ ሀገሩ አስተዳዳሪ አስጠርተውን ለምን እንደታሰርን ጠየቁን። ወንጌልን እንድንሰብክላቸው ያስቻለን አጋጣሚ ነበርና፣ የከሰሱን አካሎች ፈጥነው ሚሽኖች ናቸው ችግር እየፈጠሩብንም ናቸው የሚል ክስ አቀረቡብን።

የክፍለ ሀገሩ አስተዳዳሪ ወደ እኛ ሲመለከቱ መጽሐፍ ቅዱሶቻችንን ይዘን ሲያዩን በጣም ተቆጡ። እነዚህ ሰዎች ኢትዮጵያውያን ናቸው እንጂ የውጪ አገር ሚስዮናውያን አይደሉም። እንዴት ሚሽን ብላችሁ ትጠሩዋቸዋላችሁ? እነዚህ ሰዎች ሕግ ተላልፈዋል? ወንጀል ሠርተዋል? አሏቸውና ወደ እኛ መለስ ብለው።

ምን እንደምናስተምር ጠየቁን። ሁላችንም የራሳችን የሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ይዘን ሲያዩን በጣም ተነኩ። በዚያን ጊዜ አዲስ ክርስቲያን ማንበብ ባይችል እንኳን የራሱን መጽሐፍ ቅዱስ ለመግዛት የሚቻለውን ሁሉ ያደርግ ነበር።

ስለ ኢየሱስ ስቅለት የሚናገረውን ቴፕ ስንከፍትላቸው ሁሉም ስሜታቸው ተነካ። የተለያዩ ጥቅሶችን ከመጽሐፍ ቅዱሴ ሳነብላቸው የት እንደተማርኩ ለማወቅ ጠየቁኝ። እኔም በአለታ ወንዶ ኤስ.አይ.ኤም ት/ቤት እንደተማርኩ ነገርኳቸው። ከአለታ ወንዶ ኤስ.አይ.ኤም ጋር የነበረን ግንኙነት የሚረዳን ይሁን የሚጎዳን አላውቅም ነበር።

«ወንጀለኞች አይደላችሁም ወደየቤታችሁ ትመለሳላችሁ» ብለው ነገሩን። የክፍለ ሀገሩ አስተዳዳሪ እኔን፣ «መጽሐፍ ቅዱስ የሚናገረውን የምታውቅ ይመስልሃል? ምንም አታውቅም። እኛ እንደ መልአክ ክንፍ ያላቸውና ወደ ሰማይ ደርሰው የሚመለሱ አስተማሪዎች አሉን። ወደ አለታ ወንዶ ሂድና እዚያ ሆነህ ስበክ፣ ወይ ወደ ይርጋለም፣ ወይ ወደ ዲላ ሂድ፣ በገጠር አካባቢ መስበክ አይፈቀድልህም፣ ከእንግዲህ ወዲያ በገጠሩ አካባቢ ስትሰብክ ከተገኘህ ትገረፋለህ» አሉኝ።

በዚህ አነጋገራቸው ምንም አልፈራሁም ግን ፈገግ ብዬ ራሴን አነቃነቅኩኝ። ትዕዛዛቸውን ለመፈፀም ግን አላስገደዱንም። ወዲያው ወደ ለኩ በአስቸኳይ ፖሊስ ተልኮ ልብሶቻችንን እንዲያመጣ ትዕዛዝ ሰጡ። ሁላችንም

ወደየማረፊያ ክፍላችን እንድንገባና ሰኞ ዕለት እንድንመለስ ተነገረን፡፡ በተባለው ሰኞ ከአለቃ ወንዶ ኤስ.አይ.ኤም ሚስተር ዴልማር እስቲቨንስ መጡ፡፡ የጠራቸው የፖሊስ አዛዥ በመጥፎ ቃላት ሰደባቸው፡፡ እርሳቸውም በድንጋጤ ሕሊናቸውን ሊስቱ ነበር፡፡ እሥር ቤት ሊያስገቧቸው ቢያስቡም፣ በኋላ ግን ሦስት መቶ ብር ቀጥተው ለቀቋቸው፡፡

ልብሶቻችንን እንዳመጡልን ወደየቤታችን እንድንሄድ ለቀቁን፡፡ ምንም በወረቀት አላስፈረሙንም፡፡ ጉዳያችን ሁሉ በተለመደው ማስፈራሪያ ተደመደመ፡፡ እኛ የወሰድነው ማስታወሻም አልነበረም፡፡ ወዲያው ወደ አርኬ እንደተመለስኩ ስብከቴን ጀመርኩ፡፡

## ሁለተኛው የባለሥልጣን ተቃውሞ

ለሁለተኛ ጊዜ የታሰርኩት በ1953 ዓ.ም በብርጋድየር ጄኔራል መንግሥቱ ንዋይ ንቅናቄ ጊዜ ነበር፡፡ በዚያን ወቅት ስባት ወር ከዘጠኝ ቀን ታስሬአለሁ፡፡

ያ የመንግሥት ግልበጣ ከብዙ ዓመታት አገዛዝ በኋላ በአፄ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት ላይ የተሞከረ ሕዝባዊ ተቃውሞ ነበር፡፡ በዚያን ጊዜ አብዛኛው ሕዝብ ስለ ፖለቲካ ንቃት አልነበረውምና ገለልተኛ ሆኖ የሚከሰተውን ሁሉ በዝምታ ይከታተል ነበር፡፡ በወቅቱ በአካባቢያችን አውጫጭኝ ይበዛል፤ ያ ማለት በህብረተሰቡ መካከል ወንጀል ከተሠራ ወንጀለኛው ማን እንደሆነ ሕዝቡ እንዲያጋልጥ የሚደረግበት ዘዴ ነው፡፡

ያ አጋጣሚ ባለሥልጣኖቹ ከህዝብ ገንዘብ እንዲያገኙ ሰበብ ይሆንላቸዋል ማለት ነው፡፡ ሕዝቡን ማረጋጋት የሚችሉትም እነርሱ ናቸው፡፡

አንዳንድ የመንግሥት ባለሥልጣኖች ይህን ችግር የሚያመጡባችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ የሚያምኑ ሰዎች ናቸው ብለው ያስወሩብን ነበር፡፡ አሁንም ሰድስታችንን አሰሩን፡፡ ሦስታችን ከአካባቢው ስንሆን፣ ሦስቱ ደግሞ ከቆላማው ምድር አካባቢ የመጡ ናቸው፡፡ ወዲያው ወደ ይርጋለም እሥር ቤት ወሰዱን፡፡

## ክሶች

ባለሥልጣኖች እኛን በመቃወም የተለያዩ ክሶችን አስባስበዋል፡፡ ሁሉም የክስ ምክንያቶች ለእኛ አዲስ አልነበሩም፡፡ ደጋግመን ከምንሰማቸው ሁለቱ፡- «ሚስዮኑ ሌላ መንግሥት ሊመሠርት ነው ብለው ይሰብካሉ»፣ «ታቦትን አይቀበሉም ወይም አይፈልጉም» የሚሉ ነበሩ፡፡ ምንም የማያውቁ ሰዎች በሐሰት እንዲመሰክሩብን ያስገድዱ ነበር፡፡ ለዚህ ሁሉ ክብደት የሚሰጥ አልነበረም፡፡ ተቃውሞን ክርስቲያኖች ለረዥም ጊዜያት የተለማመዱት ስለሆነ



ከባለሥልጣኖቹ የሚቀርብላቸውን ጥያቄ አይፈሩም ነበር፡፡ ክርስቲያኖች ያላቸውን መንፈሳዊ ነፃነት ባለሥልጣኖቹ አልተገነዘቡም፡፡

በእሥር ቤት እንደነበርን ከፍተኛ አውሎ ነፋስ በእሥር ቤቱ ሕንፃ ላይ ወረደ፡፡ በዚያ አደጋ አራት እሥረኞች ሲሞቱ፣ ሦስቱ ከወላይታ የመጡ ክርስቲያኖች ነበሩ፡፡ ያ ክስተት ለእኛ ከፍተኛ ክብርን አስገኝቶልናል፡፡ እኛ ባንጐዳም አያሌ እሥረኞች አነስተኛ ጉዳት ደርሶባቸዋል፡፡ ብዙ የተለያዩ ሰዎች ያ አደጋ የደረሰባቸው በራሳቸው ስህተት ምክንያት ነው ብለው የተረጐሙ ነበሩ፡፡

## የእሥር ቤት ስብከት

ታስሬ እሥር ቤት የገባሁት በወንጌል ስብከቴ ምክንያት ነው፡፡ ነገር ግን የወህኒ ቤቱ ኃላፊዎች ለእሥረኞቹ ስስብክላቸው አልተቃወሙኝም፡፡ እንዲያውም ፈደል እያስተማርኩ እንድሰብክ የተለየ ክፍል ሰጥተውኛል፡፡

በየቀኑ የምንዘምርበት፣ የምንፀልይበትና ቃሉን የምንማርበት ጊዜ ነበረን፡፡ ብዙዎቹ በክርስቶስ የማያምኑ ሰዎች እየገቡ የወንጌልን ስብከት እየሰሙ በኢየሱስ ክርስቶስ አምነዋል፡፡

በየሳምንቱ እሁድ እዚያው ምዕዋት እየለበስብን መረዳት ለሚገባቸው ለሌሎች እሥረኞች እንሰጥ ነበር፡፡ በተለይም ከወላይታ የመጡትን ሃያ አንድ እሥረኞች በገንዘብ እንረዳቸው ነበር፡፡

እንረዳቸው የነበሩት ከእኛ ይልቅ ከቤታቸው በጣም ርቀው መጥተው የታሰሩ ስለሆነና ተጨማሪ ነገር ስለሌላቸው ነው፡፡

ያኔ የቀረበብን ክስ ከባድ አልነበረም፡፡ የክሱ ምክንያቶች የውሸት መሆናቸውን ማንም የሚያውቀው ቢሆንም፣ ከእሥር ለመፈታት ግን የተወሳሰቡ ቅደም ተከተሎችን ማለፍ ያስፈልጋል፡፡

እያንዳንዱ ባለሥልጣን የደረጃ ዕድገት ስለሚፈልግ ቀላል ክሶችን የያዙ ሰነዶች ቢመጡለት እንኳን ለበታቾቹ አስተላልፎ ለማስጨረስ አይፈልግም፡፡

እኛ በበኩላችን ሁሉንም ክሶች አልተቀበልንም፡፡ የቀረቡብንን ክሶች ለማስተባበል ከአንደበታችን ስዎችን የሚያስከፋ ቃል እንዳልተናገርን ማስረጃ አቀረብን፡፡ በእያንዳንዱ ችሎት ፊት ወንጌልን ለመስበክ ጥሩ አጋጣሚዎች ነበሩን፡፡ እኔ ሁልጊዜ መጽሐፍ ቅዱሴን እይባለሁ፡፡ ለሚቀርቡልኝም ጥያቄዎች ጥቅስ እያነበብኩ ለመመለስ እሞክር ነበር፡፡ ሁልጊዜ ከጥቅሱ ማንበቤን ዳኞች ባይደግፉም፣ ለተጠየቅኩት ጥያቄ መልስ መስጠት ስለነበረብኝ ይፈቅዱልኛል፡፡ እንደሌሎቹ ሰዎች ምክንያቶች የእኛም ምክንያት ወደ ቤት እስኪመልሱን ድረስ በቀስታ ይከስም ነበር፡፡

# በአብዮታዊ ለውጥ ጊዜ ከ1966 - 1983

ያ ጊዜ ለእኔ በቀላሉ የማልታይበት ጊዜ የተፈጠረልኝ ወቅት በመሆኑ አምላኬን አመሰግናለሁ:: ሰዎች ስለ እኔ ምንም የሚይዙት ማስታወሻ አልነበረም:: አስቀድሜ እሠራ የነበረውን ሥራ ለማከናወን ከቦታ ወደ ቦታ እዘዋወራለሁ:: አንድ ጊዜ ለሙሉ ቀን ለጥያቄ ብለው ይዘው አቆይተውኛል:: ነገር ግን የደረሰብኝ ክፉ ነገር አልነበረም::

ካድሬው በለኩ ወንጌላዊ ሆኜ እንደምሰብክ ያውቀኛል:: ግን ለጥያቄ እንደሚፈልገኝ ነግሮኝ ወደ ቢሮው ወሰደኝ:: ቀኑ እሁድ ስለነበረ የበላዮቹ በዚያ ቀን ስለማይሠሩ አቤቱታውን የሚሰማ አልነበረምና ፀረ አብዮተኛ ብሎ ለአንድ ቀን ይዞ አቆየኝ::

ወደ ማታ አካባቢ አላስፈላጊ ጥያቄዎችን እያቀረበብኝና ባዶ ምርመራ ካካሄደብኝ በኋላ ወደ ቤቴ እንድመለስ ነገረኝ:: በሌላ ጊዜ በችግር ላይ ትወድቃለህ አለኝ::

በአብዮታዊ ለውጥ ወቅት ከ1966-1983 ብዙ ክርስቲያኖች በፈጠራ ክሶች ተከስሰው ታስረዋል:: ብዙዎቹ በለኩ ለቀናትና ለሳምንት በየካድሬዎቹ ቢሮዎች ተንከራተዋል:: እኛም ለክርስቲያኖቹ ምግብ እንወስድላቸዋለን:: ለማያምኑትና ምግብ ላመጡላቸው ቤተሰቦቻቸው ወንጌልን እንሰብክላቸው ነበር:: የሚያስደንቀው ነገር ቢኖር ምንም ክርስቲያን በፀረ አብዮት ድርጊት አልተሳተፈም ነበር::

እግዚአብሔር ለቃሉ እውነት እንድንቆምና ለመንግሥትም እንድንታመን አስችሎናል:: እኔም ያለ ሥራ በቤቴ አልተቀመጥኩም:: ወንጌልንም እየተዘዋወርኩ እንዳልሰብክ ሊያግደኝ የቻለ ማንም አልነበረም:: የኢየሱስ ትምህርት በማቴ. 10፥16 ያለው አይረሳኝም፣ « እነሆ፣ እኔ እንደ በጎች በተኩላዎች መካከል እልካችኋለሁ፤ ስለዚህ እንደ እባብ ልባሞች እንደ ርግብም የዋሆች ሁኑ» ይላል::

ለወንጌላውያን ማመን ማለት የመጽሐፍ ቅዱስን መልዕክት መስማትና መቀበል ማለት ነው:: በሚሰብኩበት ጊዜ መጽሐፍ ቅዱሳቸው አይለያቸውም::

መታወቅ ያለበት አንዱ ነገር ያላመኑት ሰዎች የሚመጡት ወደ አምልኮት ቦታ ስለተጋበዙ፣ ወይም ከአዲስ ማህበረሰብ ጋር ስለተሳተፉ አይደለም:: ንስሐ መግባትና በኢየሱስ ክርስቶስ ማመን የመጣው በቀጥታ ከመጽሐፍ ቅዱስ ነው::



አዳዲስ ክርስቲያኖች መጽሐፍ ቅዱስ እንዲገዙና እንዲያነቡ ይበረታታሉ:: በዚህ በመጀመሪያው ትውልድ ቤተክርስቲያን መጽሐፍ ቅዱስ የተፈቀደው ለካህናት ብቻ አይደለም:: መጽሐፍ ቅዱስ ግልጽ መጽሐፍ ነው:: ማንም ሊገዛውና ሊያነበው ይችላል:: ማንም ሰው መንፈስ ቅዱስ ያለውን ሰምቶ ለሌላው የሰማውን ማካፈል አለበት::

መጽሐፍ ቅዱስ የሚለውን ለመተግበር ማንም ሰው የሌላው የበላይ ሊሆን አይችልም:: የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ክርስቲያኖች ለማያምኑት በሚያሳዩት ባህርይ ይወሰናል:: እግዚአብሔር ሁሉን እንደሚወድ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል:: ከእምነት ውጪ ያሉትን እንዲወዱና ወንጌልንም እንዲሰብኩላቸው ሁለቱንም እንዲፈጽሙ ታዝዘዋልና ማድረግ አለባቸው::

ከታሪኩ እንዳየነው ክርስቲያኖች በሕይወታቸው የተለማመዱት ሁሉ ከመጽሐፍ ቅዱስ የመነጨ ነው:: ጌታ ኢየሱስ በሕይወታቸውና በስብከታቸው የመጀመሪያና የበላይ ስለመሆኑ ምንም ጥርጣሬ የለም:: ለአገልግሎታቸው ክንውን የበላዩ መጽሐፍ ቅዱስ ነው:: በመጀመሪያው ቤተክርስቲያን ዕድገት ሂደት ውስጥ ባህል ከወደኋላ በማህበረሰቡ ህይወት ውስጥ መጫወት ከሚገባው ሚና ያነሰ ነው::

# ምዕራፍ አሥራ ሦስት
# ማጠቃለያ ከብራየን ፋርገር

በመጀመሪያው ትውልድ ቤተክርስቲያን ውስጥ ስለ ተዘዋዋሪ ወንጌላዊ የተካተተውን ገለፃ በማንበብ እንደተደሰታችሁ ተስፋ አለኝ።

እያንዳንዱ የአካባቢው ማህበር የመጀመሪያው ትውልድ በረከትና የመጀመሪያው አገልግሎት ተጠቃሚ ሊሆን ይችላል። ምናልባት ሆኗልም። እያንዳንዱ ቤተክርስቲያን የመጀመሪያው ትውልድ ቤተክርስቲያን ቢሆንስ? ትክክለኛና ግልጽ የሆነ ማጠቃለያ ከታሪኩ መሳል እንችላለን። ለባቱን ለይቼ ማመልከት እፈልጋለሁ። እናንተም ምናልባት ሌሎች ነጥቦችን መጨመር ትችላላችሁ።

## 1. ማመን በመጽሐፍ ቅዱስ የተመሠረተ ነው

በመጀመሪያ ቃል ነበረ፦

ክርስቲያን ያልሆኑ ሰዎች በመጀመሪያ ስለ ኢየሱስ ሲሰሙ ሁልጊዜ የሚያዩት ወንጌላዊ ተሸክሞ የሚሄደውን፣ ሲሰብክ የሚያነብበውን ትልቅ መጽሐፍ ነው።

በአንድ በኩል በባህላዊ መንገድ ተገቢ ያልሆነና የማይስማማ ነው። የሰሜናዊ ሲዳማ ባህል መጽሐፍ ይዞ የመዘዋወር ባህል አይደለም። ነገር ግን ወንጌላውያን ከዚሁ መጽሐፍ የሚሰብኩትን መልዕክት መከተሉ ጥቅም አለው። መጽሐፍ ቅዱስ፣ «እንደ ጅምራቸው መልዕክታቸውን ቀጥለው ጨረሱት» ይላል።

በኢየሱስ ክርስቶስ የማያምኑ ሰዎች ስለ መጽሐፍ የሚገምቱት ግምት ወንጌላዊውን የሚመለከት አይደለም። የሚያምኑትም ሆነ የማያምኑት በተመሳሳዩ የመጽሐፍ ቅዱስን አባባል በሁለት መንገድ ያረጋግጡ ነበር። አንደኛ፣ የሕይወት ለውጥ ሲመጣ የመጽሐፍ ቅዱስን እውነተኛነት ያረጋግጣል።

ወንጌላዊው በልበ ሙሉነት መስበክ ይገባዋል፣ ምክንያቱም ወንጌላውያን በየግል ሕይወታቸው ውስጥ እውነተኛውን ለውጥ ስለተለማመዱት ነው። ሁለተኛ፣ ከሰይጣን እሥራት ነፃ መውጣታቸውን ሲያረጋግጡ ኢየሱስ እንደሚያድን ይናገራሉ።

## 2. መጽሐፍ ቅዱስ ስብከትን ያመነጫል

ስንከታተለው በቆየነው ታሪክ ውስጥ ስብከት የራሱ የሆነ ትርጉም አለው። በዚህ በመጀመሪያው ትውልድ ቤተክርስቲያን ስብከት ማለት የክርስቶስ ታሪክ



መዋቅራዊ አቀራረብ ማለት ነው። ስብከት ማለት ያረጀውንና ለዘመናት የቆየውን እውነተኛ ታሪክ መደጋገም ማለት ነው።

የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ የመጀመሪያው ክፍለ ዘመን ቤተክርስቲያን ስብከትን እንዴት እንደተጠቀመች ያመለክታል። ከተለያዩ ስብከት ዓይነቶች ግልጽ የሆነ ግለታሪክንና ልዩነትን ማሳየትና መጠበቅ ይቻላል። ሰዎች የግል ታሪካቸውን ለስብከታቸው መሠረት አድርገው አይጠቀሙም። አንደኛ፣ የራሳቸው ሕይወት መለወጡን ለሰዎች መናገር አያስፈልጋቸውም፤ የተለወጠ ሕይወት ራሱ ይናገራል።

የሕይወታቸው መለወጥ በሁሉ ዘንድ ግልጽ ነው። ሁለተኛ፣ የግል ልምዳቸውን ለማዳበር ወንጌልን ለሌሎች ለመስበክ ልምድ ካደረጉ በቂ ይሆናል፣ ሌላ አሣማኝ ነገር አያስፈልግም። የሕይወት ለውጥ እራሱ ለማሳመን በቂ ማስረጃ ይሆናል።

በስብከት ሊቅ የሆነ ሰው የለም። በርካታዎች ግን ለስብከት ታላቅ ፍላጎት አላቸው። እያንዳንዱ አማኝ ወንጌልን በመስበክ መዋቅር መሳተፍ ይችላል። ለምሳሌ ሮሜ 15፥3-6 ላይ፣ «ክርስቶስ ራሱን ደስ አላሰኘምና፣ ነገር ግን፦ አንተን የነቀፉበት ነቀፋ ወደቀብኝ ተብሎ እንደ ተጻፈ ሆነበት። በመጽናትና መጻሕፍት በሚሰጡት መጽናናት ተስፋ ይሆንልን ዘንድ አስቀድሞ የተጻፈው ሁሉ ለትምህርታችን ተጽፎአልና። በአንድ ልብ ሆናችሁ በአንድ አፍ እግዚአብሔርን፣ እርሱም የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አባት፣ ታከብሩ ዘንድ፣ የትዕግሥትና የመጽናናት አምላክ እንደ ክርስቶስ ኢየሱስ ፈቃድ እርስ በርሳችሁ በአንድ አሳብ መሆንን ይስጣችሁ» የሚለውን ጥቅስ ፍሬ ነገሩን በአጭር ለማቅረብ ማጥናት ያስፈልጋል።

ይህ የጥንቷን ቤተ ክርስቲያን ባህርይ ይመስላል። በሐዋ. ሥራ 8፥4 ላይ፣ «የተበተኑትም ቃሉን እየሰበኩ ዞሩ» ይላል።

## 3. የስብከት ውጤት አዳዲስ ቤተክርስቲያኖችን ያስገኛል

ለጥንት ክርስቲያኖች የማያምኑትን ሰዎች ወደ ቤተክርስቲያን እንዲመጡ መመልመል ለእነርሱ የማይታወቅ ሃሳብ ነው። የማያምኑትን ሰዎች በማባበል ወደ አምልኮት ለማምጣት የሚያስብ የለም። እንደዚያ ለማድረግ ቢሞክሩ የማያምኑት ፈጥነው ተስፋ ይቆርጣሉ።

ወንጌልን የሰማ ሁሉ በግል እንዲጠቀም ይፈልጋሉ። የማያምኑት ሰዎች ከክርስቲያኖች ህብረተሰብ ጋር ከማመናቸው አስቀድመው ህብረት ለማድረግ ፍላጎት የላቸውም።

በሌላ መልኩ ደግሞ ድብቅ አማኝ የለም። የእምነት ሊቅ የሚባለው በሕዝብ ፊት የሚያምን ነው። ይህም ማለት በአንድ መንገድ ለራሱ እየኖረ፣ በሌላ መንገድ ለኢየሱስ መኖርን መቀበል ማለት ነው። በኢየሱስ ክርስቶስ ማመን ማለት የክርስቲያኖች ህብረት አካል መሆን ማለት ነው።

የስብከት ውጤቱ አዳዲስ አማኞችን ማፍራትና አዳዲስ ቤተክርስቲያኖችን መትከል ማለት ነው። ግን የስብከት ዓላማ ቤተክርስቲያንን ለመትከል ብቻ ሳይሆን፣ እያንዳንዱ ክርስቲያን በህይወት ዘመኑ ሳያቋርጥ የሚያከናውነው ልምምድ ነው።

አዳዲስ ክርስቲያኖች በክርስቶስ ካመኑ በኋላ ምን ይደረጋሉ? ገዛም ተብለው በመንፈስ ቅዱስ እጅ ይሁኑ መባል አለባቸው ወይ? እነርሱን አዲስ ቤተክርስቲያን መሥርቱ የሚላቸው የለም። ይህ ዘዴ ኢየሱስ በማቴ. 6፣33 የተናገረውን ያንፀባርቃል። «ነገር ግን አስቀድማችሁ የእግዚአብሔርን መንግሥት ጽድቁንም ፈልጉ፣ ይህም ሁሉ ይጨመርላችኋል» ብሏል።

የዚህ ዓይነት ተመሳሳይ ስብከት የችር ስጦታን ተግባር ይመስላል። ሰዎች የሚሰጡት ከጨካኝነትና ከስግብግብነት ነፃ ለመውጣት ብለው አይደለም። ሰዎች ስጦታ ሲሰጡ ከመስገብገብ ፍርሃት ነፃ ለመውጣት ነው። ታማኝነትም እንደዚሁ ነው።

ሰዎች ታማኝ ህብረተሰብ ለመፍጠር ታማኝ መሆንን አይመርጡም። ታማኝነት ግን እምነትን ያስከትላል። ያም ህብረተሰቡ አንዱ በአንዱ ላይ እምነት እንዲኖረው ያደርጋል።

የጥንት ክርስቲያኖች መልዕክቱን አይካፈሉም ወይም ገለጻ አያደርጉም፣ ግን ይሰብካሉ። ኢየሱስ ማን እንደሆነና ወደ ዓለም ለምን እንደመጣ አዋቅረው በመልዕክት መልክ ያቀርባሉ።

በሐዋ. ሥራ 8 ላይ ክርስቲያኖችን በተመለከተ ያነበባችሁት ታሪክ በሙያቸው ልምድ ያላቸውና ትጉህ ተዘዋዋሪ ሰባኪዎች መሆናቸውን ያሳያል።

ክርስቲያኖችን በትህትና የሚያስጠነቅቁ ሊቆች አልነበሩም። የማያምኑትን ሰዎች ወደ እኛ አምጧቸውና እኛ እንሰብክላቸዋለን የሚሉም አልነበሩም። ወንጌል በማን፣ መቼና የት እንደሚሰበክ የሚቆጣጠር አስተዳደራዊ መዋቅር አልነበራቸውም።

ክርስቲያኖች ሁሉም ወደሚፈልጉት ቦታዎች እየተዘዋወሩ ወንጌልን የመስበክ ሙሉ ነፃነት ነበራቸው። ምንን መስበክ እንዳለባቸውና እንዴት መስበክ እንደሚገባቸው የሚነግሩ ሊቆች አልነበሩም። በርግጥ ማጉረምረም



በብዙዎቹ ዘንድ መኖሩ ባያጠራጥርም፣ ያላመኑ ሰዎች ግን ወንጌልን ሰምተው በኢየሱስ ክርስቶስ አምነዋል።

መጽሐፍ ቅዱስ ያዘለው የደህንነት ወንጌል ለሁሉም ሰው ነው። በቃል መግለጽ ወይም በማስረዳት መስበክ ግን የክርስቲያኖች ሃላፊነት ነው። ምክንያቱም የብዙዎቹ ሕይወት በመለወጡ ብዙዎቹ ቃሉን ለማስተላለፍ ጉጉዎች ናቸው።

በተመሳሳዩ በዚህ በአዲሱ ትውልድ የቤተክርስቲያን ሰዎች አዳዲስ ቤተክርስቲያኖችን ለመመሥረት አይሰብኩም፣ ነገር ግን የስብከት ውጤት ቤተክርስቲያንን ያስገኛል።

ክርስቲያኖች የሚሰብኩት ሰዎች በኢየሱስ ክርስቶስ እንዲያምኑ ነው። ደረጃ ሁለት ግን የተለየ ነው። በኢየሱስ ክርስቶስ የሚያምኑት አዲስ ቤተክርስቲያንን ይተክላሉ።

የአዲስ ቤተክርስቲያንና የተዘዋዋሪ ወንጌላውያን ግንኙነት የማይታይ ቢሆንም፣ ግን በጣም ተጨባጭና እውነተኛ ነው። አንዳንድ ጊዜ ግንኙነት ሊኖር ቢችልም ተያይዞ የሚታይ ግን አይደለም። ለምሳሌ፣ በሰማርያ ሲዳማ ይህን ቤተክርስቲያን የመሠረተው ወንጌላዊ የትኛው ነው? አይባልም። ምክንያቱም ተዘዋዋሪ ወንጌላውያን እንደ ቤተክርስቲያን ተካይ አይታዩም። በታማኝነትና በትጋት ግን የቃሉን ዘር በመዝራታቸው ቤተክርስቲያን በብዛት ልትበቅል ችላለች። እግዚአብሔር ይመስገን!!

በተመሳሳይ መንገድ በአብዮታዊ ለውጥ ወቅት በብዙ መቶዎች የሚቆጠሩ መዝሙሮች ተደርሰዋል። መዝሙሮቹን ማን እንደጻፉቸው አይታወቅም። የባለቤቱ ስም አይጻፍም። አንዱ ይዘራል፣ አንዱ ውኃ ያጠጣል፣ አንዱ ይኮተኩታል፣ ዘሪውም ከእነዚህ ቡድን አንዱ ነው።

## 4. ቤተክርስቲያን መትከል ማለት አዲስ ማህበራዊ ቡድን ማደራጀት ነው

የቤተክርስቲያን ተክል አዲሱ ህብረተሰብ ነው እንጂ ሰዎች መሠረታዊ አድርገው የሚያመልኩበት ቦታ አይደለም። ሰዎች እግዚአብሔርን በአንድነት ያመልካሉ፤ ምክንያቱም በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን አንድ ማህበረሰብ ስለሆኑ ነው እንጂ፤ የአዲሱ ማህበራዊ ቡድን ክፍሎች ስለሆኑ አይደለም። ይህ የቤተክርስቲያን አዲስ ተክል የተከፈተ መጽሐፍ ነበረው አንድ ሰው መሬቱን ሰጠ፣ በቦታው የፀሎት ቤት ተሠራበት፣ ያንን መሬት የሰጠው ግለሰብ የአዲሱ ማህበረሰብ መሪና ሽማግሌ ሆነ። ነገር ግን ሥልጣኑ መንፈሳዊ አልነበረም። መንፈሳዊ ሥልጣን በሁሉም አማኞች ዘንድ በአንድ ቦታ ተወስኖ የሚኖር ነው። ክርስቲያን አንዱ ለሌላው ይሰብካል። አንዱም አንዱን

ያበረታታል። አንዱም አንዱን ይገሥጻል። በሐዋ. ሥራ ምዕራፍ 2 ላይ እንደነበረችው የመጀመሪያ ቤተክርስቲያን አብረው ይመገባሉ። ምግብን መስጠትና መቀበል አንድ ማህበረሰብ ካደረጓቸው ነገሮች ዋነኞቹ ናቸው።

ከእምነት ውጪ ያሉትም መጥተው እንዲበሉ ይጋበዛሉ። የራሳቸውን ምግብ ግን አያመጡም። ክርስቲያኖች የጋራ ግብ ስላላቸው አንድ ማህበረሰብ ሰመሆን በቅተዋል። መዘመራቸው፣ መፀለያቸውና ቃሉን ማስተማራቸው የማህበረሰባዊ ሕይወታቸው አስፈላጊ አካል ነበር።

ይህ የጋራ ተሳትፎ ግባቸውን አጠናክሮታል። የእግዚአብሔርን ኃይል በግልጽ በሚያሳይ ሕይወት ውስጥ መኖር ይፈልጋሉ። እንዲሁም ደግሞ ሌሎች ወንጌልን እንዲሰሙ ይፈልጋሉ። ክርስቲያኖች አንድ ማህበረሰብ የሆኑበት ምክንያት ከማህበራቸው ይልቅ የአንድ ትልቅ ነገር አካል ስለሆኑ ነው። የክርስቶስ አካል!

ይህ አዲሱ ማህበረሰብ ራሱን በራሱ የሚያስተዳድር ነው። በተወሰነ ደረጃ የማህበረሰቡን የስብከት ባህል ያከብራል። ልክ አንድ ሕፃን ገና እንደተወለደ የቤተሰቡ አባል እንደሚሆን፣ አንድ አዲስ ክርስቲያን የትልቁ ማህበረሰብ ወይም የቤተክርስቲያን አባል ይሆናል።

አዲስ ቤተክርስቲያን በተመሠረተች ወቅት አዳዲሶቹ ምዕመናን በማህበረሰቡ ላይ ይጨመራሉ።

## 5. ማህበረሰብ የሚራባ ነው

በመጀመሪያው ትውልድ ቤተክርስቲያን ማህበረሰብ ውስጥ ዕድገታችን ፈጣን ነበር። እናጠናክረው ወይም እናዳብረው የማይባል የተሟላ ዕድገት ይታይ ነበር።

ስጥንት ክርስቲያኖች አንዱ የአንዱን ሸክም የመሸከምና አንዱ ስሌላው የመጨነቅ ባህርያቸው ስሜትን የሚቀሰቅስ ነበር። እያንዳንዱን አዲስ ክርስቲያን መንከባከብ የአንድ ግለሰብ ኃላፊነት አልነበረም። የማህበረሰቡ አጠቃላይ ዓላማ ሰማደግና ሌላ ማህበረሰብ ለማፍራት ነው።

እኛ ገና ወጣቶች ነን፣ ፍሬ ለማፍራት ሙሉ ለሙሉ ያላደግንና ያልጠነከርን ነን፣ የእኛን ቡድን ወደ ሌላ ቦታ ልከን አዲስ ማህበረሰብ ሰመመሥረት በቂ ገንዘብ የለንም የሚሉትን አባባሎች በፍፁም አልሰማቸውም።

የመራባት ብቃታቸው የሚለካው በእጃቸው በሚገኝ የገንዘብ መጠን አልነበረም። እነርሱ በሐዋርያት ሥራ ውስጥ እንደነበሩት ክርስቲያኖች ናቸው



«እኛስ ያየነውንና የሰማነውን ከመናገር ዝም ማለት አንችልም» (የሐዋ. ሥራ 4÷20)።

ስብከታቸውን ማቆም አልቻሉም። የስብከታቸውም ውጤት አዲስ ማህበረሰብን ማፍራት ነበር። ክርስቲያኖች በሰበኩ ቁጥር ይራባሉ። ሁሉም ማህበረሰብ ይህን ያደርጋል ብሎ መገመት ሃሳባዊ ያሰኛል። ምንም ያህል ደካማ ድምፅ ቢያሰሙ ማንም አያውቅም፣ ማንም አይጨነቅም። ነገር ግን የሚዘሩት ቃል በየቦታው ይበቅላል።

የመጀመሪያው የገንዘብ ሃላፊነታቸው ሁልጊዜ ስብከት ነው። ከዛሬ ሃምሳ ዓመት መጀመሪያ አካባቢ ማንም ሰባኪ ለእሁድ አገልግሎቱ ከቤተክርስቲያን ገንዘብ አይቀበልም።

የእሁድ ጧት የስጦታ ገንዘብ ኢየሱስ ጌታ መሆኑን ለሚያውጁት ተዘዋዋሪ ወንጌላውያን ይሰጣል።

በሰሜናዊ ሲዳማ የቤተክርስቲያን ተክል በጥንቃቄ የሚቆጣጠሩት ዓይነት አልነበረም። አንድ ሃላፊነት የሚሰማው ሰው በራሱ ሃሳብ አፍላቂነት የቤተክርስቲያን ሽማግሌዎች ሳይሰሙ በየሳምንቱ ሐሙስ ጧት ከተወሰኑ ምዕመናን ጋር የፀሎት ፕሮግራም ቢጀምር ይህ አዲስ ቤተክርስቲያን ነው ብሎ የሚገምት አይኖርም። ይህ እንግዲህ ሲሆንም ላይሆንም ይችላል፣ የሚወሰነውም እንደ አካባቢው ሕዝብ ፍላጐት እንጂ፣ የሐሙስን ፕሮግራም በፍላጐቱ ጀምሮ በሚመራው ሰው የሚወሰን አይደለም።

በወቅቱ ቤተክርስቲያን መመሥረት አስባት ብሎ የወሰነ አልነበረም። የሐሙስ ጧት የፀሎት ጊዜ ሰዎች ተሰባስበው ሲበራከቱ ወደ እሁድ አገልግሎት ይለወጣል። ይህም የሚሆነው የሚሰበሰቡበት የቤቱ ባለቤት የፀሎት ቤት መሥሪያ መሬት ከራሱ መሬት ቆርሶ ለመስጠት ፈቃደኛ ከሆነና እሁድ እሁድ መንፈሳዊ አገልግሎት ለመጀመር ከተስማማ ነው።

ይህን ለማድረግ ሐቁ ወንጌልን ለመስበክ ያለ ፍላጐትና ጽኑ ምኞት በአካባቢው አማኞች ስሜት ውስጥ ሲኖር ነው። አዲስ ቤተክርስቲያን የአንድ ሰው አዕምሮ ሃሳብ ውጤት አይደለችም። የተወሰነ ቁጥር ያላቸው ሰዎች ለመስበክ ፍቃደኛ የሆኑ ከሌሉ ቤተክርስቲያን በፍፁም አታድግም፣ ትቀጭጫለች እንጂ።

## 6. መራባት እንክብካቤን ይጨምራል

«የእናንተ ጉዳይ የእኛ ጉዳይ ነው» ማለት የአዲሱ ማህበረሰብ መመሪያ ነው። በተቀራረበ ማህበረሰብ ውስጥ ምሥጢር የለም። አንዱ አንዱን ይንከባከባል፣ እርስ በርስ ለመረዳዳት ጣልቃ እየገቡ መሥዋዕትነት ይከፍላሉ።

አዲሱን ማህበረሰብ ልዩ የሚያደርገው ድርሻው ነው:: ይህ ማለት ክርስቲያኖች እርስ በርስ የመረዳዳት ድርሻ አላቸው:: ለአዳዲስ ምዕመናን ከፍተኛ እንክብካቤ ያደርጋሉ፣ ፈጣን ምላሽ በመስጠትም በጥንቃቄ ይቆጣጠሯቸዋል:: ከሌላው ሕብረተሰብ እንኳን እየመጡ አዲሱን ማህበረሰብ ያግዙ ነበር::

አንዳንዶች ከሥነ ምግባር ጉድለታቸው፣ ከሚያሰክር መጠጥ፣ ከፀያፍ ንግግርና ስድብ ለመላቀቅ ችግር ነበረባቸው:: እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት በህብረተሰቡ መካከል ሥር የሰደዱ ልማዶች ናቸው:: ማንም ሊደብቃቸው የማይችላቸው ነገሮች ሲሆኑ፣ ሕዝቡም ሊያጠፋቸው ባለመቻሉ እየታገለ ነው::

ፀሎት አዲስ ሲሆን፣ በአሮጌው ባህል እንደ ፀሎት ያለ ነገር አልነበረም:: ወይም የፀሎት ልምድ አልነበራቸውም:: አሁን ግን በፀሎት ለእግዚአብሔር ይናገራሉ፣ እግዚአብሔርም ይመልሳል፣ ለእርስ በርስም ይፀልያሉ::

## 7. መንከባከብ ወደ ሙላት ይመራል

እንክብካቤያቸው ሁሉም ሰው ወንጌልን እንዲሰማ ያላቸውን ምኞት በግልጽ የሚያሳይ ነበር:: ስለሆነም ብዙ ሰዎች በኢየሱስ ክርስቶስ ሊያምኑ ችለዋል::

አቶ ሶርሳ ዛሬ በሰሜናዊ ሲዳማ ሰባ ከመቶ የሚሆኑ ሰዎች ክርስቲያኖች ሆነዋል ያሉትን አባባል የተጋነነ ነው ብዬ እጠራጠራለሁ:: ነገር ግን የልብ ምታቸውን የሚያንፀባርቅ ስሜት እንደሆነም አምናለሁ:: እያንዳንዱ ሰው በጌታ ኢየሱስ እስኪያምን ድረስ ወንጌልን መስማት! መስማት! መስማት! አለበት::

አቶ ሶርሳና መሰሎቻቸው ቃሉን ወደየድንበሮች አዳርሰዋል:: የአካባቢ ማህበራት ተዘዋዋሪ ወንጌላዊያን በየማህበረሰቡ መካከል ተቀጥረው ይሰብካሉ:: ሌሎች ተዘዋዋሪ ወንጌላውያን ግን በኢየሱስ ክርስቶስ የሚያምኑ ሰዎች ወደሌሉበት አካባቢ እየተዘዋወሩ ይሰብካሉ::

ይህንን ለማስፋፋት ማንም ተቀምጦ እቅድ እንዳላወጣ ማስታወስ ያስፈልጋል:: የመጀመሪያ ትውልድ ምዕመናን የመንፈሳዊ ሕይወት ውጤት ሆነዋል:: ያ ውጤት የተመሠረተው ወንጌልን በመስበክ ነው::

ለአንድ ሳምንትና ለወር ካየናቸው በኋላ ወንጌላውያኑ ለሌሎቹ ይህን ያህል አይጨነቁም እንል ይሆናል:: ነገር ግን በእያንዳንዱ ሳምንትና ወር እድገቶች ይኖራሉ:: በየጊዜው የቁጥር ዕድገት ይታይ ነበር:: በአምሳ ዓመት አገልግሎት ውስጥ የአራት መቶ ማህበራትን የማፍራት ውጤት ታይቷል::



በማህበረሰቡ ውስጥ ስራ ሥራ ተከማችቶልናል:: እያንዳንዱ ሰው በመረጠው መንገድ መልስ ለመስጠት አጋጣሚ ነበረው:: የሚሰበክለት ሰው እስካለ ድረስና ወንጌል ከተሰበከለት በኢየሱስ የማመን አመቺነት አለው:: ስለዚህ እንሰብካለን የሚል ዋና ዘዴያቸው ነበር:: ወንጌልን ለመስበክ አንድ መንገድ ብቻ ነበራቸው፣ ያም ከአንዱ ሰው ለሌላው ሰው መስበክ ነው::

## አራት ዋና ጭብጥ መልዕክቶች

ስለ ታሪኩ ከፖውል ባሊስኪ ጋር ስንወያይ አንባቢ በአዕምሮው ውስጥ ሊያስቀምጣቸው ስለሚገባቸው ስለ አራት ዋና ጭብጦች አመለከቱኝ::

እያንዳንዱ መልዕክት ስለ አቶ ሶርሳ ሱማሞ ተዘዋዋሪ ወንጌላዊነትና በክርስቶስ አካል ውስጥ ተስማሚ ስለሆኑት ሰው ስለ አቶ ሶርሳ አገልግሎት ያወሳል::

## ገንዘብ

በተለያዩ ጊዜያቶች አቶ ሶርሳ ሱማሞ ከሲዳማ ወይም ከወላይታ ማህበራት አበል ይቀበሉ ነበር:: ነገር ግን ከማህበሩ የሚያገኙትን ገንዘብ ተስፋ አድርገው አልኖሩም:: ያ ይሰጣቸው የነበረ ገንዘብ እንደ ደሞዝ ሳይሆን ጊዜያዊ ስጦታ ነበር::

አቶ ሶርሳ በደመወዝ ያስመቀጠራቸው ወደፈለጉበት አካባቢ እየሄዱ ለማገልገል ነፃነት ሰጥቷቸዋል:: ስለዚህም የቦርዱ አመራሮች ወዲህና ወዲያ ሂድ የሚል መመሪያ አይሰጧቸውም::

የክርስቶስ ስም ባልተጠራበት ቦታ ሁሉ ወንጌልን ለመስበክ ጽኑ አቋም ባይኖራቸው ኖሮ አቀራረባቸው ዛላፊነት የማይሰማው ይሆን ነበር እንደዚያ ግን አልነበረም::

አቶ ሶርሳ ከአዳዲስ ማህበራት አንዳንድ ነገሮችን ለመቀበል ቀዳሚ አይሆኑም:: በእርግጥ የሚሰጣቸውን ስጦታ የሚቀበሉበት ወቅቶች ነበሩ:: እሁድ እሁድ ከሚሰበሰበው የምፅዋት ገንዘብ የተወሰነ ድርሻ የሚሰጣቸው ምክንያቶች ነበሩ:: ታዲያ ለአንድ ጊዜ ብቻ የሚሰጣቸው እንጂ በየወሩ የሚሰጣቸው አልነበረምና በቤተክርስቲያን አስተዳደር ገብተው እንዲታሠሩ አያስገድዷቸውም:: እርሳቸውም ተሸምተው ለመግባት አይፈልጉም ነበር::

የሁለት ሺህ ዓመት ቤተክርስቲያን ታሪክ የሚያሳየው በአንድ የአገልግሎት መስክ ላይ የተለየ ትኩረት መስጠት የሚመጣው በቤተክርስቲያን አስተዳደር ሥር እንደሆነ እንስማማለን:: ተዘዋዋሪ ወንጌላዊ እንደ ልቡ እየተዘዋወረ ሲሰብክ ውጤቱ የበለጠ ስኬታማ ሊሆን ይችላል::

ለአንዳንዶች መዘዋወር ሃላፊነት የጐደለው ሥራ ሆኖ ሊታይ ይችላል:: ነገር ግን የተዘዋዋሪ ወንጌላዊ ተስማሚ ባህርይ ነው::

## ዕውቅና ማግኘት

ሰብዙ ሰዎች ዕውቅና ከፍተኛ ማነቃቃት የሚያገኙበት ሲሆን፣ ያ ዓላማ ግን ወደ ስንፍና የሚያመራቸው ነው:: ሁላችንም ሰዎች ስንሆን፣ ሰዎች መሆናችን ደግሞ ተፈጥሮአዊ ክስተት ነው::

ተዘዋዋሪ ወንጌላዊና አቶ ሶርሳ ሱማሞ በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን መስመር ላይ የሚጓዙ ሁለት ገጽታዎች ናቸው:: እነርሱም ወንጌልን ለሰዎች ለመስበክ ምኞታቸው ከፍተኛ ሲሆን፣ ተራራ ሰመውጣት ትልቅ ፍላጐት እንዳለው ሰው ዓይነት ስሜት ነበራቸው:: ተራራ ወጪዎች በጣም ረዥም ወደሆነው ተራራ በመውጣት ሕይወታቸውን በአደጋ ላይ የሚጥሉት ለምንድን ነው?

ምክንያቱም አስቀድሞ ሌላ ሰው ወጥቶ ስለማያውቅ ለመቅደምና ዝና ለማትረፍ ነው:: የኦሎምፒክ ሠልጣኞች አራት ዓመት ሙሉ በድካም ሠልጥነው ካሸነፉ በኋላ አነስተኛ ወርቅ የሚሸለሙት ለምንድን ነው? ምክንያቱም በዓለም ታዋቂ ሆነው ለመታየት ነው:: ጥልቅ ፍቅርን ለማሳየትና ለማሳካት ብቸኛው ገለጻ ይህ ነው::

ተዘዋዋሪ ወንጌላዊ ገንዘብ፣ የእጅ ጭብጨባ፣ ማዕረግና ሽልማት አይፈልግም:: እርሱ የሚፈልገው ወንጌልን ያልሰሙትን ሰዎች ፈልጐ ማሰማት ብቻ ነው:: ተዘዋዋሪ ወንጌላዊ በሥራው በፍፁም አይረካም:: ሁልጊዜ በዓይነ ሕሊናው ወንጌልን ሊሰሙ የሚፈልጉትን ሰዎች ያስሳል::

ሰዎች ትኩረት ቢሰጧቸውም ባይሰጧቸውም፣ቢሸልሟቸውም ባይሸልሟቸውም፣ ዕውቅና ቢሰጧቸውም ባይሰጧቸውም ምንም አይጨነቅም:: እርካታ የሚያገኘው ወንጌልን ሰምቶ የማያውቅ ሰው ወንጌልን ሰምቶ ማመኑን ሲያይ ነው፣ የሚፈልገውም ያንን ብቻ ነው::

አቶ ሶርሳ የተለየ የስብከት ጽናታቸውና የረዥም ዓመታት አገልግሎታቸው በግልጽ የሚታይ ቢሆንም፣ ጡረታ ለመውጣት ወይም ከወላይታና ከሲዳማ ማህበራት ወይም ከኤስ ኣይ ኤም ዕውቅና ማግኘት ጐልቶ አይታያቸውም ነበር::

እንዲሁም ከሰዎች ጥቅም ለማግኘት ሩጫ አያደርጉም:: አንድ ነገር ከተሰጣቸው ምናልባት ፈገግ ብለው ከእኔ የበለጠ የሚገባቸው አሉና ለእነርሱ ስጧቸው ይሉ ነበር::



## አስተዳደር

አቶ ሶርሳ ሱማሞ በማህበሩ አስተዳደር መዋቅር ውስጥ ለመሳተፍ ምንም ፍላጐት ወይም ምኞት አልነበራቸውም:: አብዛኛዎቹ ሰዎች ግን ከሌሎች እንክብካቤና ክብር ለማግኘት የሥራ ደረጃ ይፈልጋሉ::

ኘሬዘዳንት ወይም ሊቀመንበር ወይም ጀኔራል ልሁን ከዚያም ነገሮችን ሁሉ የበለጠ አሻሽላለሁ ማለት የብዙዎች ምኞት ነው:: ያንን ፍላጐትና ክብር በሕሊናቸው ውስጥ በማሳደር አያሌዎች ወደ ፖለቲካ ዓለም ገብተዋል::

ተበዋዋሪ ወንጌላዊ ግን በአስተዳደራዊ መዋቅር በኩል ለሚደረገው መሻሻል ጀርባውን ይሰጣል::

አቶ ሶርሳ ለአዳዲስ ማህበራት ቋሚ ሆነው በአስተዳደር መዋቅር ውስጥ መሳተፍን አይፈልጉም:: በማህበሩ መካከል የቡድን ተሳትፎ አላቸው:: ነገር ግን የእርሳቸው ጥልቅ ፍቅር ወንጌልን ለማስቀደም በመካከላቸው እየሰበኩ መመላለስ ነው::

የትም ለመሄድ ፍቃድ መጠየቅ አልነበረባቸውም:: የአካባቢ ሰዎች የበለጠ ሥልጣን እንዳላቸው በማሰብ ልመና አያቀርቡም:: በሥራቸው ወደ ኋላ ስለማይመለሱ ሰዎች ራሳቸውን አደራጅተው ሥራቸውን ይቀጥላሉ::

አዲስ ቡድን የቤተክርስቲያን ተክል ሲሆን ካልቻለም የእርሳቸው ጭንቀት አይደለም:: ነገር ግን ትተዋቸው ወደ ሌላ አካባቢ በመሄድ ይሰብካሉ:: አዲስ ቤተክርስቲያን መትከል የእርሳቸው ኃላፊነት አይደለም::

ይህም ማለት በማንኛውም ደረጃ ከነበሩ የቤተክርስቲያን አስተዳደር ጋር ምንም ቶክክር አልነበራቸውም ማለት ነው:: በአቶ ሶርሳ ልምድ ውስጥ በአስተዳደር ቦታ ያሉትን የሚያጽናኑበትና የሚያበረታቱበት ጊዜ ነበራቸው ፣ ያ ግን ሌላ ምዕራፍ ነው::

ለአስተዳደር ፍላጐት እንዳይኖራቸው ነፃነትን ለጥቷቸዋል:: ተዘዋዋሪ ወንጌላዊ በአገልግሎቱ የሰለጠነና ልዩ ሙያተኛ በመሆን ሌሎች ሲሠሩ የማይችሉትን ይሠራል:: ለመውጣትና ለመውደቅ የሚያስችል የአስተዳደር መሰላል የለውም::

## ፍርሃት

አቶ ሶርሳ እግዚአብሔር የፈለገውን እንዳይሰሩ የሚያግዳቸውን ፍርሃት ፈቅደው አይቀበሉትም:: በፍፁም አይፈሩም ተብሎ ቢጠቃለል ይመረጣል::

መንፈሳዊ ኃይሎችንም አይፈሩም:: ክርስቶስ ፍርሃትን በመስቀል ላይ እንዳሸነፈው ይተማመናሉ:: አንዳንድ ሰዎች ይረግሟቸው ይሆናል?

ካጋጠማቸውም በመሳቅ አሳልፈው መንገዳቸውን ይቀጥላሉ:: በቁጣና በስድብ ራሳቸውን ቤተሰባቸውን፣ ከብቶቻቸውን ፣ እርሻቸውን ይረግማሉ ወይ? ይህ ሲያጋጥማቸው ትርጉም የለሽ መሆኑን በመገንዘብ ወደ ጢሻ እንደ መወርወር ቆጥረው ይተዉታል::

በክርስቶስ ስም ድልን ያውቃሉ:: የሚሸነፍ መንፈሳዊ ኃይል እንዳለም ያረጋግጥላቸዋል::

አቶ ሶርሳ በሃምሳ ዓመት አገልግሎታቸው ከክፉት መንፈሳውያን ሠራዊት ችግሮችን ተጋፍጠዋል:: ነገር ግን በፍፁም አልፈሯቸውም:: በዚያን ዘመን ከኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን እምነት ተከታዮችና ከሙስሊሞችም በየጊዜው ፈተና ቢደርስባቸውም ፍርሃት አላሳዩም ነበር::

ለደህንነታቸው እንኳን አስጊ የሆነ ነገር ሲያጋጥማቸው፣ የሚፈሩት ነገር አልነበረም:: አቶ ሶርሳ ትልቅ ቤተሰብ ያላቸው ሲሆን፣ ቤተሰባቸውን የመንከባከብ ሃላፊነት ቢኖርባቸውም፣ የሚያስፈልጋቸውን ሁሉ እግዚአብሔር እንዲያሟላላቸው ወደ እርሱ ይመለከታሉ:: እርሳቸው ግን በእግዚአብሔር እርሻ ላይ ዘር መዝራታቸውን ይቀጥላሉ::

# የመጨረሻ ቃል

# ከአባባ ሶርሳ ሱማሞ

ለእኔ የተለወጠ ሰውን ከማየት የበለጠ ፈጽሞ የሚያስደስተኝ ነገር የለም:: አዳዲስ ክርስቲያኖች ለክርስቶስ ሲዘምሩ ሳይ ልቤ በሐሴት ይሞላል:: የምዕመናኑ ዝማሬ አንድ ነገር ነው:: እኔ ለማየት የምፈልገው የማያምኑት አምነው ተለውጠው ሲዘምሩ ነው::

አዳዲስ ሰዎች በኢየሱስ ክርስቶስ ሲያምኑ፣ መንፈስ ቅዱስ ሕይወታቸውን ሲለውጥ በቃላት ከምናገረው በላይ ያስደስተኛል:: በእግዚአብሔር ኃይል በእውነት የተለወጡ ሰዎችን ማየት ምድራዊ ገነት ነው::

በሰይጣን የሚሰቃዩና የሚጐሳቆሉ እንዲሁም ወደ ሲዖል ይሄዱ የነበሩ ሰዎች አሁን እግዚአብሔር ይመስገን በማለት ወደ ሰማያዊ ጉዳና ሲያቀኑ ልቤ የቆመ እስኪመስል በደስታ እሞላለሁ::

# የፍላጎት አቅርቦት

የጳውሎስ እናት (ባለቤታቸው ማለት ነው) በሲዳማ የቤተክርስቲያን ታዋቂ የምግብ አዘጋጅ ነበረች፤ መስተንግዶዋ በቅርብም በሩቅም ይታወቃል:: በየቀኑ እንግዶች ወደ ቤታችን እየመጡ ይጎበኙናል፣ ምግብም እንሰጣቸዋለን:: ሁልጊዜ ለሁሉም የሚበቃ ምግብ ከቤታችን አይጠፋም::



የየቀን ወጪያችንን ለመሸፈን በጣም ጠንክራ ትሰራለች:: ወደ ይርባ ገበያ እየሄደች በቆሎ ትገዛና እቤት በባህላዊ ወፍጮ በእጅዋ ትፈጫለች፣ ከዱቄቱም ለቤተሰባችንና ለእንግዶቻችን ዳቦ ትጋግርልን ነበር:: የተረፈውን ደግሞ ትሸጣለች:: ጥጥ እየፈተለችም በመሸጥ ተጨማሪ ገንዘብ ለቤት ወጪያችን ታመጣልናለች::

እግዚአብሔር ሁልጊዜ ከምንፈልገው በላይ ይሰጠን ነበር:: የምንፈልገውን ሁሉ በብዛት እናገኛለን:: ልጆቻችንም ተርበው አያውቁም::ጥሩ ልብስም እንለብሳለን ከአካባቢዬ ህብረተሰብ መካከል የበታች ሆኜ አላውቅም:: የምንታመምበት ጊዜያቶች ቢኖሩም፣ የባሰ ሕመም አላጋጠመንም::

እኔ ነጋዴ አልነበርኩም:: ያለኝን ጊዜ ሁሉ በእርሻዬ ላይ አላሳልፍም:: በፊልጵስዩስ የተጠቀሰውን የእግዚአብሔርን እውነት ደጋግመን አረጋግጠናል:: «እንግዲህ በእኛ እንደሚሰራው ኃይል መጠን ከምንለምነው ወይም ከምናስበው ሁሉ ይልቅ እጅግ አብልጦ ሊያደርግ ለሚቻለው፣ ለእርሱ በቤተክርስቲያን በክርስቶስ ኢየሱስ እስከ ትውልዶች ሁሉ ከዘላለም እስከ ዘላለም ክብር ይሁን፤ አሜን» (ኤፌ. 3÷20–21)::

በተጨማሪም:–«አምላኬም እንደ ባለጠግነቱ መጠን በክብር በክርስቶስ ኢየሱስ የሚያስፈልጋችሁን ሁሉ ይሞላባችኋል::ለአምላካችንና ለአባታችንም እስከ ዘላለም ድረስ ክብር ይሁን፤ አሜን» (ፊልጵስዩስ 4÷19–20)::

በብዙ የተለያዩ ቦታዎች ያሉት ምዕመናን ስላደረጉልን ብዙ ነገሮች አመሰግናቸዋለሁ:: ብዙ ጊዜ እርሻዬን በማረስ ያግዙኛል:: የሲዳማ ማህበር ምንም ነገር አይሰጠኝም፤ ሰዎች እህል እንዲሰጡኝ ለመጠበቅ ራሴን አላስገድድም:: በቂ ምግብ የላቸውም ብለው በማሰብ ሰዎች እህል ሰጥተውን አያውቁም::

እኔ ተግቼ እሰራ ስለነበር እግዚአብሔር ደግሞ ያለንን ሁሉ ባርኮ ስለሰጠን ተቸግረን አናውቅም:: ከስብከት አገልግሎቴ አስራ አንድ ሰዓት ወደ ቤቴ እንደገባሁ ልብሴን ቀይሬ የስራ ልብስ እለብስና እስኪጨልም እርሻዬን አርሳለሁ::

አንዳንድ ጊዜ ሲጨልም ትንሹን ፋኖስ እጠቀማለሁ:: በአንድ ምሽት በጨለማ ውስጥ ሳርስ ልሞት ነበር:: አንድ ጎረቤቴ በመንገድ ሲሄድ በዛፍ አጠገብ የፉጨት ድምፅ ሰማሁ:: ጃርት መሆኑን አላስተዋልኩም:: ያ ጎረቤቴ ወደ ጨለማ ሲመለከት እኔ የማንኮሻኩሸውን ድምፅ ሰምቶ ትልቅ ጃርት መስዬው ኖሮ ኮሽታ ወደ ሰማበት አቅጣጫ ጦሩን ለመወርወር ተዘጋጅቶ አደፈጠ:: በቀስታ እየቀረበኝ ሲመጣ እኔ መሆኔን አወቀ:: ወዲያው በሆነው ሁሉ እፍረት ተሰምቶት አንዳች ቃል ሳይናገር ወደ መጣበት ተመለሰ:: በሌላ

ጊዜ ጦሬን ወርውሬ ልወጋህ ምንም አልቀረኝም ብሎ ነገረኝ። ስላለን ጥበቃና እንክብካቤ እግዚአብሔር ክብር ይሁን እንላለን።

## ፍቅር

ለአገልግሎት ያነሳሳኝና እንድቀጥልበትም ያደረገኝ የጌታ ፍቅር ነው። እግዚአብሔር እንደወደዳቸው እኔም ሰዎችን ከልቤ የመውደድ ስሜት አሰኝ። ሁልጊዜ ከልቤ፣ «እነዚህን ሰዎች እግዚአብሔር በጣም ከወደዳቸው እኔም እነርሱን መውደድ ይገባኛል» ብዬ አስባለሁ።

ይህ ፍቅር ከህይወቴ ከሚወስድብኝና ከሚጠፋብኝ ስብከቴን ባቆም ይሻለኛል። ያለፍቅር የሚሰበክ ስብከት ፍሬአልባ ነው። «የክርስቶስ ፍቅር ግድ ይለኛል» (2 ቆሮ. 5÷14)።

ይህ ፍቅር ነው ስለ ኢየሱስ ለሰዎች እንድናገር የሚያስገድደኝ። ፍርድ እንዳለ አውቃለሁ÷ ለሰዎች ፍርድ እንዳይደርስባቸው አስጠነቅቃቸዋለሁ፡ የምናገራቸውም ምክንያት በጣም ስለምወዳቸው ነው።

ፍቅር ማለት ማንኛውንም ነገር ለማየት የሚያስችል እንደ ተራራ ጫፍ ነው። አዎን፣ እግዚአብሔር እንደወደደኝ አውቃለሁ። ስለ ፍቅሩ በማስብበት ጊዜ ሁሉም ነገር ያስደንቀኛል።

## ተጨማሪ 1

የእስቲቨንስ ቤተሰብ በደቡባዊ ሲዳማ፡-

ይህ መግለጫ የዶልማርና ሜሪ እስቲቬንስ የመጀመሪያ ሁለት ጊዜ ማለትም በቅድሚያ በናይጀሪያ ቀጥሎም በኢትዮጵያ በአዲስ አበባ ውስጥ ቀጥሎም በሲዳሞ ክፍለ አገር በአለታ ወንዶ ወረዳ በመሆን ስላሳለፉት ጊዜ የተሰጠ ነው።

በሊንኮልን ኔብራስካ በመገናኛ ብዙሃን መጽሐፍት ቅዱስን በምናስተምርበት ጊዜ የኤስ አይ ኤም ሚስዮናውያን በሆኑት በጎርደን ቤከሃምና በካርል ታኒስ በሬድዮ ጣቢያችን እንግዳ ተናጋሪዎች ሆነው በመጡበት ሃሳብ ቀረበልን።

ያቀረቡልንም ሃሳብ «ጌታን ለማገልገልና ወንጌልን ለማሰራጨት ሰፊ አጋጣሚ በተዘረጋበት አገር የሚሲዮናዊ እጥረት አጋጥሞናል» ካሉን በኋላ ሄደን እንድንሰራ ለመኑን። በቅንነት ከፀለይንበት በኋላ እግዚአብሔር በራሱ ጊዜና እንደ ራሱ ፈቃድ እንዲልከን እርሱን በመተማመን በእምነት ተራመድን። በወቅቱ ሱዳን ኢንተርየር ሚስዮን በተባለ ድርጅት ሥር ሚስዮናውያን ሆነን እንድንሄድ ተቀባይነትን አገኘን።



ጥሪያችን ወደ ኢትዮጵያ ቢመስለንም ለመጀመሪያ ወደ ናይጀሪያ ተላክን ፤ ምክንያቱም ወደ ኢትዮጵያ ለመግባት የመግቢያ ፈቃድ በእጃችን አልገባም ነበር። በኢትዮጵያ ጊዜው የጣሊያን ጦርነት ነበርና መንገደኞች በፖርቹጋል መርከብ ከፍላደልፊያ ወደ ሊዝቦን ተነሳን። በቁጥር ሰላሳ የምንሆን የኤስ አይ ኤም ሚስዮናውያን ቡድን ስንሆን ጆን ዋንዳርችና ሬይ ዴቪስ የቡድኑ መሪዎች ነበሩ።

ለስድስት ሳምንት በሊዝቦን ከቆየን በኋላ ሌላ የፖርቹጋል መርከብ ይዘን ወደ አንጎላ በኮንጎ ወንዝ ሄድን።ከዚያም በጀልባና በባቡር ወደ ሊዎፓልድቪል ቤልጂየም ኮንጎ ገባን።

በመጨረሻም በቻርተርድ አውሮፕላን ወደ ሌጎስ ናይጀሪያ በረርን። ሁላችንም የቋንቋ ት/ቤታችን ወደሆነው ወደ ሚና በባቡር ተጓዝን።

ከትንሽ ጊዜ በኋላ ወደ ኢትዮጵያ እንደምንሔድ ስለምናውቅ የሀውሳ ቋንቋ እየተማርን በናይጀሪያ ጊዜያችንን ማጥፋት አልነበረብንም።

የነበረንን ስሜት በጊዜው በጆስ ለሚገኙትና የኤስ አይ ኤም ዳይሬክተር ለነበሩት ለሚስተር አሊቬር በጽሑፍ ካስታወቅን በኋላ፣ እርሳቸውም ወደ ጆስ ሄደን የቢሮ ስራ እየሰራን እንድንቆይ መመሪያ ሰጡን።

ስለሆነም በጊዜው ስራ አስኪያጅ የነበሩት ጌሪና ዶራቲ ስዋንክ እንደ ፍላጎታቸው በእኛ ፋንታ በሚስዮኑ ጣቢያ እንዲሰሩ አስችሏቸዋል።

እኛ ወደ ኢትዮጵያ ለመግባት ፍቃዳችንን እስክናገኝ ድረስ ለዘጠኝ ወር በጆስ የቢሮ ስራ እየሰራን አሳልፈናል። ከካኖ ወደ ካርቱም በረርንና በኤስ አይ ኤም ዋና ጽ/ቤት ከሃውዋርድና ሩዝ ቦርለዝ ጋር ቆየን። ከዚያም በባቡርና በአውቶቢስ ወደ ኤርትራ አስመራ ደረስን።

የኤስ አይ ኤም ሚስዮን ከአዲስ አበባ ስቴሽን ዋገን መኪና ላከልን። ከአስመራ ወደ ምጽዋ ሊቶሪና በሚባለው መኪና ተጓዝን። የተላከልንን የስቴሽን ዋገን ይዘን ወደ አስመራ እየተመለስን ከአስመራም በብሪቲሽ ወታደራዊ ኮንቮይ ወደ አዲስ አበባ ተጓዝን። የደረስነውም በ 1937 ዓ.ም በፀደይ ነበር።

በአዲስ አበባ ውስጥ አማርኛ አጠናን። ለአያሌ ወራትም በአሮጌው ጽ/ቤታችን የቆየነው ከፒያሳ ውጪ ሙሴ ሚናስ ቤት ይባል በነበረ ቦታ ነው። ሚስተር ጎርደን ቤክሀም የመጀመሪያ ዳይሬክተር ሲሆኑ፣ በኋላም በጂም ሉክማን ተተክተዋል። በመጨረሻም ሚስተር ግሌን ዳይሬክተር ሆነዋል።

እንድንሰራ የተመደበልን ቦታ ሆማኞ ሲሆን፣ ይህ የቀድሞው ጣቢያ በግሌን ቃየንና በአልፍ ሮክ ከጣሊያን ወረራ በፊት ተከፍቶ ነበር:: በ1937–1938 ዓ.ም ከአልፍ ሮክና ከሆመር ዊልሰን ጋር ደልማር ከወላይታ ወደ ሲዳሞ በ1935 ሞዴል የሚስዮኑ መኪና ሁለት ጊዜ ጉዞ አድርገዋል::

በጉዞአቸውም ላይ በየመንገዱ ጉማ እየፈነዳባቸው በብዙ መከራ አልፈዋል::ከጣሊያን ወረራ በኋላ ጎማ ወዲያው ለመግዛት አይቻልም ነበር::

ያንን ጉዞ ያደረግንበት አብይ ምክንያት የሲዳማን ህዝብ ለመገናኘትና በሲዳማ ውስጥ በሆማኞ ሚስዮን ጣቢያ አቋቁመን ልንሰራ ስለምንችልበት ሁኔታ ለመወያየትና ሁኔታዎችን ለማመቻቸት ነበር:: ያ ጉዞ በብዙ አቅጣጫ በጣም ውጤታማ ነበር:: ከጣሊያን ወረራ በኋላ የኢትዮጵያ መንገዶች በጣም ተበላሽተው ነበር:: ብዙ ድልድዮች ፈራርሰዋል:: ሀገሪቱም በእግሯ ወደኋላ መራመድ ጀምራ ነበር:: ከቦታ ወደ ቦታ መዘዋወርና መሥራት አይቻልም:: መደበኛ ንግድም ቆሞ ነበር: ከጎማ እጥረት የተነሳ መኪናዎች አይንቀሳቀሱም፣ ደግሞም የመለዋወጫ እቃ አልነበረም:: በየመንገዱም ብዙ የመኪና ግጭቶችም ነበሩ::

ደልማር ታዋቂ የጎማ ለጣፊ ሆነው ተመረጡ:: ቆይተውም በዚሁ ሙያ የሰለጠኑና ብቁ ሆነዋል:: በብዙ አጋጣሚዎች ያረጁ ጎማዎች የሚጣፉት መንቀሳቀስ ወደማይችሉበት ደረጃ ሲደርሱ ነበር::

በተጨማሪም የተወሰነ የአማርኛ ቋንቋ ችሎታቸውን በየመንገዱ የተጠቀሙ ሲሆን፣ ጥሩ ልምድም አካብተዋል:: በጊዜው አዲስ አበባ ጋዝ ተመጥኖ የሚሰጥ በመሆኑ ጋዙ በሚኖርበት ጊዜ ቀይ የፈቃድ ካርድ ይዞ በመሰለፍ ያልተወሰነ ሰዓት መጠበቅ የተለመደ ነበር::

ለአንድ ረዥም ጉዞ በቂ ነዳጅ ለማግኘት በጭቅጭቅ ሰልፍ ይዞ መቆየት የተለመደ ነበርና ሚስተር ሮክ ረዥም በርሜል ሙሉ ጋዝ በስውር ገበያ ገዝተው ይጓዙ ነበር::ጋዝ ማግኘት ይቻል ነበር:: ነገር ግን የጋዙ በርሜል ውኃ የተሞላበት ሆኖ እንዳይገኝ ብልህ ሰው ተጨማሪ ገንዘብ ይከፍላል:: በክፍለ ሀገር ያን ጊዜ ጋዝ ስለማይገኝ ከአዲስ አበባ ወደ ክፍለ ሀገር የሚጓዝ መንገደኛ ለደርሶ መልስ የሚበቃ ጋዝ ይዞ መጓዝ ይጠበቅበት ነበር::

ከአለታ ወንዶ ጥቂት ኪሎ ሜትር ብቻ አልፎ ወደ ሆማኞ ገባ ካሉ በኋላ ጋናሜ ሁንዴ የሚባለውን አንድ የኦሮሞ ሰው ተገናኙ::ይህ ሰው በጣሊያን ጊዜ የሚስተር ሮክ ረዳትና አማካሪ ነበር:: የውጭ ሚሲዮናውያን በሚሄዱበት ጊዜም ንብረታቸውን በመጠበቅ ያገለግላል::

ጋናሜና ቤተሰቡ በሲዳማ ህዝብ መካከል የሚኖሩ ኦሮሞዎች ነበሩ:: የኦሮሚኛ፣ የሲዳሚኛና የአማርኛ ቋንቋዎችን አቀላጥፈው ይናገራሉ:: ስለዚህ



በሲዳማ በቆየንባቸው ዓመታት ውስጥ ታላቅ ረዳታችን ሆኖልናል:: ጋናሜ የሚሲዮኑን ንብረት ከዘገወጥ ዘራፊዎችና ሽፍታዎች ለመታደግ ህይወቱን የሰጠ ሰው ነበር:: እርሱንና ቤተሰቡን ለመግደል ዘራፊዎች ሲያሴሩ በሰማ ጊዜ ቤተሰቡንና ከብቶቹን ይዞ ወደ ወንዶ በመግባት ከሌሎች ኦሮሞዎችና አማሮች ጋር ተቀመጠ::

እኛም ወደ ሆማኞ በተመለስን ጊዜ ግቢያችን ምስቅልቅሉ ወጥቶ የከብቶች መዋያ ከመሆኑም በላይ ምንም የተረፈን ነገር አልነበረም፤ የእኛ የሆነውን ሁሉ ዘርፈዋል:: በእነዚያ ጉዞዎች ሁሉ ከአዲስ አበባ አስተዳደራዊ ቢሮዎች ፈቃድ በማውጣት በሲዳሞ ክፍለ ሀገር ልንሰራ የምንችልበትን የሚስዮኑን የስራ ፈቃድ ማግኘት ነበረብን::

በ1939 ዓ.ም አካባቢ ሚስተር ሮክ ሁላታችንንም ወደ ሆማኞ ወሰዱን:: ያም የምንቆይበት ስፍራችን ነበር:: ጉዞው በጠቅላላው ሳምንት የፈጀብን ሲሆን፣ በመንገዳችንም በተደጋጋሚ ጎማ እየፈነዳብን እየጣፍን ተጓዝናል::

በሆማኞ ግቢያችን ውስጥ የሳር ክዳን ቤትና በቆርቆሮ የተሸፈነ ወጥ ቤት በአፋጣኝ ተሰርቶ ተጠናቀቀልን::ወደ አዲሱ ሳር ቤታችን ብንገባም የተሻለና የተመቸን ቤት ግን አልነበረም :: ነገር ግን ብቸኛ ቦታችን ስለሆነ አማራጭ አልነበረንም፤ በዚያ ክረምት ከባድ ዝናብ ሲዘንብ አሳለፍን::

በጣሊያን ወረራ ጊዜ እነ ሮክ ሲሄዱ ማንም መደበኛ አገልግሎት አላካሄደም ነበር:: ዋናዎቹ ሽማግሌዎች የሚስዮኑን ንብረት ለመዝረፍ ቀንደኛ እንደነበሩ አወቅን፣ እነርሱ ግን ተሰወሩ::

ከአያሌ ዓመታት በኋላ ደልማር አንዱን ሽማግሌ ተገናኝተው ነበርና በክርስትና ህይወት እንዳልቆየ ተረዱ:: ነገር ግን በሚስተር ሮክ ጊዜ አምነው የነበሩት ሁለት ሰዎች በዘረፋው የተሳተፉ መሆናቸውን አጋለጠ:: ሁለቱም ሰዎች አቶ ዳዋቆና አቶ ዋቼ ይባሉ ነበር::

ለሚስተር ደልማር ሌሎች ሰዎች እንደገለጹላቸው ለሰይጣን መስዋዕት በሚደረግበት ጊዜ ፍየል ይታረድና ደሙ በሰውየው ግንባር ላይ ይረጫል:: ያም የሚያመለክተው ለሰይጣን መስዋዕት ማቅረቡን ነው:: የሲዳማ ሰዎች ይህንን ሲያደርጉ በስተመጨረሻው ደልማር ራሳቸው በዓይናቸው አይተው ነበር::

በዚያ መስዋዕት በሚሰዋበት ጊዜ አቶ ዳዋቆና አቶ ዋቼ«እኛ በክርስቶስ ደም ነጽተናል ሌላ ደም አያስፈልገንም በማለት የፍየሉ ደም በግንባራቸው እንዳይረጭ ከለከሉ:: ከዚያ በኋላ በሆማኞ ለቤተክርስቲያን እምብርት ሆነው ከማገልገላቸውም በላይ የመጀመሪያው የሆማኞ ቤተክርስቲያን ፀሎት ቤት በአቶ ዋቼ መሬት ላይ ተሰርቶ ለዓመታት ቆይቷል::

በሆማኝ ለራሳችን አነስተኛ የእንጨት ቤት ባለ ጣውላ ወለል ሆኖ በዝናብ ወቅት ጣሪያው ዝናብ እንዳያስገባ አድርገን ሰራን፡፡ በዚያን ወቅት ሚስተር ሮክና ዶ/ር ሆመር ዊልሰን በየገጠሩ እየተዘዋወሩ ለሚስዮኑ ጣቢያ የሚሆን አመቺ ቦታ ካሰሱ በኋላ በአለታ ወንዶ የሚስዮኑ ጣቢያ የሆነውን ቦታ መረጡ፡፡

ይህ አካባቢ በአለታ ወንዶ በስተሰሜን የሚገኝ ሲሆን በዋናው አውራ ጎዳና መስመር ላይ ነው፡፡ ከሆማኞ ይልቅ በቀላሉ በሚታይ ቦታ ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ የተለያዩ የፈቃድ ወረቀቶችን ከክፍለ ሀገርና ከአካባቢው አስተዳደር ካገኘን በኋላ የመሬት ኮንትራትና የመጨረሻ ውል ተፈራርመን ፀደቀልን፡፡

ወዲያው ከሆማኞ ወደ ወንዶ ተዛውረን የቤቶች ግንባታ ጀመርን፡፡ የመጀመሪያው ቤት ያሰራነው ለነርሶችና ለአስተማሪዎችን ነበር፡፡ የመጀመሪያ ነርስ የነበሩት ጎልዳ ማይ(ቤጊስ) እንዲሁም የመጀመሪያ አስተማሪ አማንዳ ሄሪን(ማንዲ)ነበሩ፡፡ ደልማር በአነስተኛ ችሎታቸው በሽተኞችን ይረዱ ነበር፡፡ ቤቶችን በአለታ ወንዶ ጣቢያችን በሰራን ጊዜ አብሮ የተሰራው ክሊኒክ ወደ ህክምና ስራ ስለተዛወረና እነ ቤጊስ ስለተረከቡት ደልማር ደስ ብሎአቸዋል፡፡ ቤጊ ምርጥ ነርስ ነበረች፡፡ ለምርመራ ይመጡ የነበሩት ሰዎች በየቀኑ እየተጨመሩ ሄዱ፡፡ ደልማርም ከቤጊስ ጋር በሳምንት አንድ ቀን ወደ ሆማኞ እየሄዱ በክሊኒክ ህክምና ያደርጉ ነበር፡፡ ሁለተኛውን ቤት የሰራነው ለራሳችን ነበር፡፡

ጆንና ሚልድሬድ ኬለርማን መጥተው በርና መስኮት በመስራት ከፍተኛ እገዛ አድርገውልናል፡፡ ለማንዲ የት/ቤት ሕንፃ ከሰራን በኋላ ከወንዶ ከተማ እየመጡ የሚማሩትን ልጆች ለማስተማር ትሞክር ነበር፡፡ በአንድ ቀን አምስት ተማሪዎች ይኖሩአታል፣ በሌላ ቀን ሌሎች አምስት ይመጡ ነበር፡፡

ሉሳ ሼፍ፣ ሉሲል ዊክስሮም፣ኢሊያኖር ፓስኬት ጂን ሮበርተንና ሉሲ ኮዊ የተባሉ አስተማሪዎች ወደ ወንዶ መጥተው እስኪያስተምሩ ድረስ የአካባቢው ልጆች በእርግጥ የትምህርት ቤታችንን ጥቅም አልተረዱም ነበር፡፡

ብዙ ልጆች ወደ ት/ቤት ይመጡ የነበረ ሲሆን፣ ወዲያው እያቋረጡ ወደየቤታቸው ይመለሱም ነበር፡፡ በየሳምንቱ እሁድ በቀርከሀ በተሰራ ጣሪያ ት/ቤታችን ህንፃ ውስጥ የእሁድ አምልኮትና ስብሰባ የጀመርን ሲሆን፣ የተደራጀ ቤተክርስቲያን ግን አልነበረም፡፡

ደልማር በየሳምንቱ ወደ ሆማኞ እየሄዱ ቢጋናሜ ቤት ቤተክርስቲያን ለመመስረት በመሞከር መንፈሳዊ መልእክት ያስተላልፉ የነበር ቢሆንም፣ አጥጋቢ ውጤት አልነበራቸውም፡፡



በመጨረሻ ግን የሲዳማ ምዕመናን ተባብረው በመሰባሰብ በአቶ ዋቼ መሬት ላይ የፀሎት ቤት ለመስራት በቅተዋል፡፡

በዚያን ጊዜ መንፈሳዊ መልዕክት ይተላለፍ የነበረው በአስተርጓሚ ሲሆን፣ ሚስተር ደልማር ስዕሎችን በመጠቀም የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮችን እያሳዩ በማስተማር በሁሉም ዘንድ ድጋፍና ውጤት ያገኙበትን አገልግሎት ያከናውኑ ነበር፡፡

ቮና ብድል በቤጊ ቦታ ተተክተው በኢትዮጵያ አብዛኛውን ጊዜያቸውን በአለታ ወንዶ ጣቢያችን ያለዓመት እረፍት አሳልፈዋል፡፡በመጨረሻዎቹ ያመታት የሲዳማን ልጆች ወደ ሶዶ በመላክ በዶ/ር ናታን ባርሎ የሚሰጠውን ረዳት የጤና ባለሙያነት ስልጠና እንዲያገኙ አድርገዋል፡፡

ስራው ከባድ እንደመሆኑ ሰልጥነው የተመለሱት ረዳት የጤና ባለሙያዎችም በአለታ ወንዶ ክሊኒክና በሆማኞ ይሰሩ ነበር፡፡ ሚስተር ደልማር የበሽተኞችን ጥርስ በመንቀል ቮናን ረድተዋል፡፡ በዘመኑ በተለይም የሸመገሉ ኢትዮጵያውያን የጥርስ ችግር ይበዛባቸው ነበር፡፡

የምንሰብከው የእውነት ወንጌል መሆኑን ቢረዱም፣ አብዛኛዎቹ ሰዎች የኦርቶዶክስ ቤተክርስትያንን ግፊት ይፈሩ ስለነበር በክርስቶስ ለማመን በግልፅ ሊወስኑ አልቻሉም፡፡

ጋናሜ ከዘመዶቹና ከጓደኞቹ ግፊት የተነሳ በእምነቱ ይዋዥቅና ይወላውል ጀመር፡፡ በመጀመሪያ ጊዜያችን ጎብኚዎች በአለታ ወንዶ ጣቢያ ከሩቅ የሚመጡና ጥቂቶች ነበሩ፡፡ የመጡትም ቤተሰቦች ቢከሃም ግሊን ቃየን ካርል ታኒስ ሲሆኑ፣ እኛን ሚስዮናውያን እንድንሆን ምክንያት የሆኑንና እግዚአብሔር የተጠቀመባቸው ነበሩ፡፡

አሌክስና ትሬሽያ ወደ ቡርጂ ሲሄዱ ጎራ ብለው ጎብኝተውንም ነበር፡፡ አልበርትና ኤቭሊን ብራንት ከልጃቸው ሐዊ ጋር የጎበኙን ሲሆን፣ እነርሱም በዲላ የኤስ አይ ኤም ጣቢያ የከፈቱት ናቸው፡፡ በቆየንባቸው ዓመታት ውስጥ በተደጋጋሚ እንገናኝ ነበር፡፡ አስቀድመን የጠቀስናቸው ሚልድሬድ ኬለርማን ለተወሰነ ጊዜ አብረውን ነበሩ፡፡ ይህ ሁሉ የነበረው መንገድ ተሻሽሎ ከመስራቱ በፊት ሲሆን፣ ወደ አዲስ አበባ ደርሶ መልስ መመላለስ የተለመደም ጊዜ ነበር፡፡ ይኬድ የነበረውም በጣሊያን ቡና ጫኝ መኪና ላይ ሲሆን፣ ጉዞው አያሌ ቀናት ይወስድ ነበር፡፡

በጣቢያችን በቆየን ጊዜ ሚስዮኑ ለአሮጌው መኪናችን ጎማዎችን ገዝቶ ሰጠን፡፡ ሆመር ዊልሰን በአዲሱ ጎማ ላይና ታች እየተመላለሱ ደልማርን ያስቀኑ ነበር፡፡

ወራት ካለፉ በኋላ በ1938 ዓ.ም ሁለት መኖሪያ ቤቶችና አንድ ክሊኒክ እንዲሁም የአለታ ወንዶ ት/ቤት የነርስና የመምህራን ቤቶች ተገነቡ:: ከነበረብን ሀላፊነት የተነሳም በጣም ስራ ይበዛብን ነበር::

ብዙ ሲዳማዎች ወንጌልን እንዲሰሙ ለማድረግ ደልማር ሳያመነቱ ምሳቸውንና የውሀ ኮዳቸውን ሸክፈው ፈረሳቸውን በመጋለብ ስስ ልብሳቸውን ልጅ በማሸከም ወደ ሆማችና ሌሎች ወረዳዎች በመዘዋወር አጋጣሚ በሚያገኙበት ቦታ ሁሉ ወንጌልን ይሰብኩ ነበር::

በአማርኛ እየተናገሩ በሲዳሚኛ ሲተረጎምላቸው ስለሚሰሙ የሲዳሚኛንም ቋንቋ ለመግባባት ያህል ችለው ነበር:: እርሳቸውም የመጀመሪያውን ወቅት ስራዎቻችንን አስመልክተው ይናገሩ ጀመር:: ቋንቋ አጥንተን የነበረው በአዲስ አበባ ነው:: ወደ ደቡብ ገጠር ተጉዘን አሮጌ ማቢያችንን በሆማች መሰረትን::

ከዚያም የአለታ ወንዶ አዲሱ ማቢያችን ኮንትራት እንደተጠናቀቀ ወደ አለታ ወንዶ ተዛወርን:: በመጀመሪያ ጊዜያችን በወንዶ በተከፈተው አዲሱ ማቢያችን የሚስዮናውያን ቤቶችን፣ ትምህርት ቤቱንና ክሊኒኩን በመገንባት፣ ተጨማሪ ቋንቋ በመለማመድ ያሳለፍንበት ከፍተኛ እንቅስቃሴና ሥራ የበዛብን ወቅት ነበር::

እንዲሁም የስራ ፍቃዳችንን ለማደስ በጊዜው የሲዳሞ ክ/ሀገር ዋና ከተማ ወደነበረው ወደ ይርጋለም በየዓመቱ በተደጋጋሚ እንመላለስ ነበር::

መንገድ ከመሰራቱ በፊት ወደ ይርጋለም በፈረስ ወይም በበቅሎ ለመጓዝ አራት ሰዓት ይፈጅብን ነበር:: በወንዶ ለመስራት የመጀመሪያውን የስራ ፈቃድ ያወጣነውም በ1938 ዓ/ም ላይ ነበር::

ለዓመት ዕረፍታችን ወደ ኒውዮርክ እንደደረስን ሜሪ ከፍተኛ ኦፕሬሽን የመሆን አጋጣሚ ቢፈጠርባትም የእረፍት ጊዜያችን ደስታ የተሞላበት ነበር:: በእረፍት ጊዜያችን ዘመዶቻችንን ከመጎብኘታችንም ሌላ ወደሚረዱን አብያተ ክርስቲያናት እየተዘዋወርን ኮንትራታችንን እናድስ ነበር:: እንዲሁም ለአንዳንድ ነገሮች የተወከልንበትን ስራዎች አከናውነን በ1942 ዓ/ም ወደ ኢትዮጵያ ተመለስን::

ስንመጣም አዲስ መኪና ገዝተናል፣ ያም በስተጀርባው መጽሐፍ ቅዱስን ለመስበክ ድምፅ ማጉያ ነበረው:: ያን አዲስ መኪና የገዛነው ለመጀመሪያችን ሲሆን 1940 ሞዴል ነበር::በዚያ አስቸጋሪ መንገድ ወጣ ገባ እያልንና ላይና ታች እየተዘዋወርን በጭቃማና ጎድጓዳ መንገዶች ወደ ወንዶ ጠርዝ ድረስ እንነዳ ነበር::



ከዚህም በተጨማሪ ደልማር ቤት ለማስከደን ረገኘም ቁጤማና ቀርከሃ በማጓጓዝ እንዲሁም በጠና የታመሙትን በሽተኞች የኖርዌጂያን ሐኪም ወዳሉበት ወደ ይርጋለም ሆስፒታል ለማመላለስ መኪናችን ከፍተኛ እገዛ አድርጓል::

አንድ ጊዜ አልበርት ብራንት ታምመው በስተኋላ መጫኛ ላይ አስተኝተዋቸው እስከ አዲስ አበባ ወስደዋቸዋል::

ሁለተኛ ረዥም ጊዜ አልቆየንም:: የወላይታ ወንጊላውያን ከወላይታ አብያተ ክርስቲያናት ተልከው መጥተው በሲዳማ ወንጌልን ለመስበክና ቤተክርስቲያን ለመመሥረት ደልማርን ተገናኙ::

ደልማርም ሲያገኙዋቸው አብረው ለመስራት በጣም ደስ አላቸው:: ሲዳማ ውስጥ እየኖሩ ቋንቋቸውን ተምረው ወንጊልን ለማሰራጨት በጨለማ ውስጥ ለሚገኙትና በሰይጣን እስር ውስጥ የነበሩትን ለመመለስ እንዲችሉና እውነተኛውን እግዚአብሔርን እንዲያመልኩ እርሱ የተጠቀመባቸው ነበሩ::

በመካከላቸው የበላይ የነበረው አቶ ሾንጋ ይባል ነበር:: እርሱም ከእኛ ጋር ለአያሌ ዓመታት ሰርቷል:: በመጨረሻ ግን ኖርዌጂያኖች በየወሩ ለሚከፍሉት ደሞዝ ተሸንፎ ሄዷል:: እነርሱም በሲዳማ ብዙ አብያተ ክርስቲያናትን እንዲመሰርቱ እግዚአብሔር ተጠቅሞባቸዋል::

በየወሩ በነበረን የቤተክርስቲያን ሽማግሌዎች ስብሰባ ደልማር ብዙ የሚያስደስቱ ሌሊቶችን ከነዚያ ሰዎች ጋር ስለ ቤተክርስቲያን ችግሮች በመመካከር ያሳልፉ ነበር::

ለሁለተኛ ጊዜያችን የክሊኒኩና የት/ቤቱ ግንባታ ተጠናቅቆ ለመማር የሚፈልጉ ተማሪዎች ማስተናገድ ከምንችለው በላይ ሆነው በዙ:: ክሊኒካችንም ሁልጊዜ በህሙማን የተሞላና የሚመረመሩም ህሙማን በብዛት ተራ የሚጠብቁበት ነበር::

ነርሷ ማከም የማትችላቸው ከባድ በሽታ የነበራቸውን ሰዎች ወደ ይርጋለም ሆስፒታል እናስወስድ ነበር:: የልብ ችግር ያለበት አንድ ሰው ወደ ክሊኒካችን በተደጋጋሚ እየመጣ ይታከም ነበር::

ሾና ብድል የሰውየውን ሁኔታ በተረዱ ጊዜ ደልማር ወደ ይርጋለም ሆስፒታል በአስቸኳይ እንዲያደርሱት አሳሰቡ:: ወዲያውም ወሰዱት፣ በጉዞአቸውም ላይ ወንጌልን ሰበኩለት:: እዚያው በይርጋለም ሆስፒታል ትተውት መጡና ከጥቂት ሳምንት በኋላ ተመልሰው ሄደው ሲያዩት ችለዋል::

የሰውየው ሁኔታ በጣም አስጊ መሆኑ የተነገራቸው ቢሆንም በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ሰላመነ ምንም የሚያስፈራው ነገር የለም አሉ::

ከጥቂት ጊዜ በኋላ ሰውየው ሞተ። ሚስተር ደልማር አስክሬኑን ከወንዶ ጣቢያችን ብዙም በማይርቅ ቦታ ወደሚገኙት ቤተሰቦቹ ዘንድ አመጡ።

ዳልማር ከጥቂት ልጆች ጋር ሆነው በቤቱ አቅራቢያ አስቀበሩት። ጓደኞቹ ጉረቤቶቹና ዘመዶቹ አልረዷቸውም። ያንን ሰው አንድ ቀን በመንግሥተ ሰማያት እንደምናየው እርግጠኞች ነን። ሰሁለተኛ ጊዜ እግዚአብሔር ያስቻለን ነገር ቢኖር ቋንቋ አጥንተን ሁለተኛ የአማርኛ ፈተና መውሰዳችን ነበር።

ጋናሜ በጣም ይረዳን የነበረ ሲሆን፣ የኢትዮጵያ አዲስ ዘመን ጋዜጣም ስልምምዳችን ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጉልናል። ያንን ከበድ ያለውን አማርኛ ለመረዳት በጣም አስቸጋሪ ቢሆንም፣ የምንችለውን ሁሉ አድርገናል። ወዲያው ለመፈተን ወደ አዲስ አበባ ሄድን ከብዙ ሚስዮናውያን ጋር ፈተናውን ወሰድን። ፈተናውን ለማለፍ የመጀመሪያዎቹ ኤስ.አይ.ኤም ሚስዮናውያን ነበርን። ፈተናውም የተሰጠን ዴቪድ ስቶክስ የብሪትሽ ቤተክርስቲያን ሚስዮን ሰሳይቲ ነው።


በመጀመሪያ ጊዜያችን እግዚአብሔር በሁለት ሴት ልጆች ባርኮናል። እነርሱም የዓመት ዕረፍት ለመውሰድ በተቃረብን ጊዜ ወደ ቢንግሃም አካዳሚ ት/ቤት ገብተዋል። ሦስተኛው ወንድ ልጃችን ለዕረፍት ወደ ሊንኮልን ኔብራስካ እንደደረስን ነበር የተወሰደው።

ከዚህ በላይ የተገለፀው ዘገባ ለእኔ ለብራዬን ፋርገር የተላከልኝ ከደልማር እስቲቨንስ በግንቦት 14 ቀን 1990 ዓ.ም ነበር። የደልማር እስቲቨንስ አድራሻም።

**1839** W. Arlington Circle,

Lincoln, NE 68522

U.S.A ነው።



የራስ አገዝ ወንጌላዊ ታሪክ ወንጌልን ለመስበክ ጥልቅ ፍቅር ስላላቸው ሰው የሚተርክ ነው። ከሃምሳ ዓመት በላይ መጽሐፍ ቅዱሳቸውን ተሸክመው በሰሜናዊ ሲዳማ ብዙ ሺ ኪሎ ሜትሮችን በመጓዝ ለሚገናኙት ሁሉ ወንጌልን ሰብከዋል። በነዚያ ዓመታት ውስጥ በአካባቢው 400 ቤተክርስቲያኖች ተመሥርተዋል።

አቶ ሶርሳ ሥራቸው ወንጌልን መስበክ ሲሆን አዳዲስ ክርስቲያኖችም ቤተክርስቲያንን እንደሚተክሉ ያምናሉ፣ እውቅና ማግኘትና የገንዘብ ሽልማት ፍላጐታቸው አይደለም። እርሳቸውን የበለጠ የሚያሳስባቸው በጨለማ ላሉት ወንጌልን ለመስበክ ከእግዚአብሔር ለቀረበላቸው ጥሪ ታማኝ ሆኖ መገኘት ነው።

ብራየንና ዶሪስ ፋርገር ከኤስ.አይ.ኤም ጋር በኢትዮጵያ ከ1950-1951-1977 ዓ.ም ድረስ ሚስዮናውያን ነበሩ። አቶ ሶርሳ ሱማሞ ወንጌልን ለመስበክ ስላላቸው ጥልቅ ፍቅር አብረው ሃሳብ ለሃሳብ ተለዋውጠዋል።

ብራዬን እና አቶ ሶርሳ ለመጀመሪያ የተገናኙት በ1951 ዓ.ም ነበር። አቶ ሶርሳም በ1993 ዓ.ም ካናዳን ጐብኝተዋል። በዚያ በካናዳ ቆይታቸውም ብራዬን አግኝተዋቸው ታሪካቸውን በአንድነት አሰባስበው ለማቅረብ መልካም አጋጣሚ ፈጥሮላቸዋል።

ይህ ታሪክ ከቦታ ወደ ቦታ እየተዘዋወሩ ወንጌልን ለሚሰብኩና ለእግዚአብሔር ጥሪ ምላሽ ለሚሰጡ ሁሉ ማበረታቻና መታሰቢያ እንዲሆን የባለታሪኩና የፀሐፊው ፀሎትና ተስፋ ነው።